በምስራቅ አፍሪካ ዳርቻ ሰማይ ላይ

ዛሬ የካቲት 6, 2011 ዓ.ም. የብርቅየው ኢትዮጵያዊ ፈላስፋ ዕጉዋለ ገብረ ዮሐንስን 87ኛ የልደት በዓል ነው። ትልቅ በዓሌ ነው:: “ልደትሰ በኩሉ ልደት፤ ጸውዐኒ በካልእ ዕለት” የማይባልበት የልደት በዓል ማክበር በጣም ደስ ያሰኛል::

ከሶስት ዓመት በፊት በዚሁ ፌስቡክ ገፄ ላይ (በተመሳሳይ ርዕስ ስር) እንዲህ ብየ ነበር፥

ይህ ታላቅ ፈላስፋ ከ 50 ዓመት በፊት ጀምሮት የነበረውን ግን ደግሞ ተዳፍኖ የቀረውን የጥንታዊት ኢትዮጵያ ስልጣኔ መነሻ ኡድርጌ የራሴ ፍልስፍናዊ እይታ ለማቅረብ እሞክራለሁ::

ያኔ ለመዳሰስ የሞከርኩት እጉዋለ “የጥንታዊት ኢትዮጵያ ስልጣኔ” ብሎ የጠራውን ምንጩን ፍልስፍናዊ በሆነ መንገድ ሰፔኩሌት ማድረግ ሲሆን፤ በዚህ ዓመት ለመዳሰስ የፈለግኩት ጉዳይ ደግሞ የእጉዋለን “በተዋህዶ ከበረ” ፕሮጀክት ላይ ሂሳዊ ምልከታ (Critique) ማቅረብን ነው።

በነገራችን ላይ ፍልስፍናዊ እይታ ሲባል የሆነ ሐሳብን እንደ መነሻ በመውሰድ የተለያዩ ተፃራሪ ሃሳቦችን እርስ በራሳቸው በሶቅራጥስ መንገድ እንዲነጋገሩ በማድረግ ወደ እውነታው ለመድረስ የሚደረግ ጥረትን ለማመልከት ነው። የሚታፊዚክስ፣ የኤፒስቲሞሎጂ፣ እና የኤቲክስ ሃሳቦችን በውስጠ ታዋቂነት ይዳሰሳሉ እንጂ ቀጥታ address አይደረጉም።

እጉዋለ ጥንታዊው የኢትዮጵያ ስልጣኔ ደርሶበት የነበረውን ከፍታ ሲገልፅ አንዲህ በሚል ቁጭት ነው፥

“በአፍሪካ ምስራቃዊ ዳርቻ የታወቀውን ስልጣኔ ለማስገኘት ብዙ ሊቃውንት ጥረዋል:: ሰማዩ ወይም ጠፈሩ ልሙጥ ነበር፤ የነዚህ ሰዎች ጥረት የሚያበሩ ከዋክብት በዚህ ጠፈር ላይ አስገኝቶአል። ምን ይሆናል ብዙ ደመና ሸፍኖአቸዋል እነሱን ለመረዳት ክንፍ ብርቱ ክንፍ ያሻል…”

እኔ ደግሞ እላለሁ፣ በአጭሩ ሲገለፅ የቀደምት ኢትዮያውያን ስልጣኔአቸው ምንጭ በፍልስፍና መነፅር ሲታይ በሰው ልጅ ተፈጥሮ ላይ የነበራቸው ጥልቅ እይታ ነው። የሸፈናቸው ደመና ደግሞ በዋናነት በአራተኛው ክፍለ ዘመን ላይ ወደ ኢትዮጵያ የገባው እና ቤተ መንግስቱን የተቆጣጠረው አትናትዮሳዊ ክርስትና ሲሆን (ብሩህ አለምነህ የብህትውና እና የተአምራታዊነት ክርስትና ብሎታል)፤ በሌላ በኩል ደግሞ በቤተ መንግስትና በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ የተሰባሰቡ ጥራዝ ነጠቅ እውቀት ላይ የተመሰረተ ሀሳብ የያዙ የ“ካህናተ ደብተራ” ምሁራን እይታዎች ብዛት ነው ::

ለዚህም በጥልቅ እውቀት ላይ የተመሰረተ እይታ የያዙትን በቅድመ ክርስትና አከሱም የነበሩትን ቀደምት ኢትዮያውያን አባቶችን እና የእነርሱን ፈለግ እና መንፈስ እየተከተሉ በዘመናት መካከል የተነሱ ሌሎች አባቶችን "ሊቃውንት" (Intellectuals) የሚለውን ስያሜ ስጠብቅላቸው፤ ይሄን ታላቅ ስልጣኔ እንዲዳከም ብሎም ተመናምኖ እንዲጠፋ በአትናትዮሳዊ ክርስትና ጦር የወጉትን እና በየዘመናቱ የስልጣኔውን መንፈስ ይዘው ለተነሱ ግለሰቦች እንግልት፣ ስደትና ሞት ምክንያት የሆኑትን ደመናዎቹን ደግሞ ምሁራን (elites) ብያቸዋለሁ::

ደመና ከመሬት ከፍ ብሎ መሬት ላይ ሆኖ ለሚመለከተው ሰው ሩቅ ሊባል በሚችል ከፍታ ላይ ያለ ሲሆን፤ ከፀሀይ ደግሞ እጅግ እጅግ በጣ.....ም ዝቅ ብሎ እንዲያውም ከፀሀይ አንፃር ሲታይ ከመሬት ጋር እኩል ሊባል በሚችል ርቀት ላይ ነው ቦታው:: በየዘመኑ ያሉ እና የነበሩ የደመና ምሁራኖችም እውቀታቸው ከተራው ሰው አንፃር ሲታይ ከፍታ ላይ ያለ ቢመስልም፣ ከፀሀዮቹ (ከዋክብት) ሊቃውንት አንፃር ሲታይ ግን አፈር ለብሶአል:: ጥቅጥቅ ያለ ደመና ለጊዜው የፀሀይ ብርሀንን እንደሚጋርድ ሁሉ፤ የነዚህ ምሁራን መብዛትም የሊቃውንቱን ብርሃን ለጊዜው ሸፍኖታል:: ሆኖም ብርቱ ሞተር ያለው የአውሮፕላን ክንፍ ጥቅጥቁን ደመና ሰንጥቆት እንደሚያልፍ ሁሉ፤ ብርቱ የህሊና ክንፍ የሆነውን ፍልስፍና የያዘ ሰውም ጥቅጥቁን የምሁራን ደመና ሰንጥቆ ከሊቃውንቱ የእውቀት ጨረር ጥበብ ሊቋዋደስ ይችላል::

በተዋህዶ ከበረ ፕሮጀክት ላይ የማቀርበውን ሂሳዊ ምልከታ በደንብ ለመረዳት ይረዳን ዘንድ መጀመሪያ እነዚህ በልሙጡ የምስራቅ አፍሪካ ሰማይ ላይ ሲያበሩ ለነበሩ ከዋክብት የስልጣኔአቸው ምንጭ የሆነውን በሰው ልጅ ተፈጥሮ ላይ የነበራቸውን ምልከታ መገለጫዎች አቀርብና፤ ቀጥሎ አሁን ላይ ስልጣኔውን የሸፈነው የ “አዳፍኔ” ደመና ምን እንደሆነ እንመለከታለን።

ሰው ምንድን ነው? (ነፃ ፈቃድ የጥንታዊው ስልጣኔ የጀርባ አጥንት)

ታላቁ ፈላስፋ አሪስጣጣሊስ (Aristotle) “ሰው ምክንያታዊ አእምሮ(rational) ያለው እንስሳ ነው” አለ:: በሌላ በኩልም “ሰው ማህበራዊ እንስሳ ነው” ይላል :: ቀደምት ኢትዮጵያውያን ሊቃውንትም ሁለቱንም ብያኔዎች (definition) ተቀብለው የራሳቸውን መሰረታዊ ነገር (element) ነፃ ፈቃድን ጨምረው እንዲህ በማለት ይገልፁታል:- “ሰው ነፃ ፈቃድ ያለው ምክንያታዊ አእምሮ የያዘ ማህበራዊ እንስሳ ነው::”

የሰው ልጅ ነፃ ፈቃድ ያለው ፍጡር መሆኑን እና በዚሁ ምክንያትም የሚጎናፀፈው የመንፈሳዊ ልዕልና ከፍታ እና ውድቀት መኖሩን ብዙ ታላላቅ ፈላስፎች ደራሲዎች የተናገሩ የፃፉ ቢሆንም ከቀደምት ኢትዮጵያውያን ፈልቀው የተፃፉ ድርሰቶች ግን በተለይም የቅድመ ክርስትና አከሱም ሁኔታን ሊያስረዱን የሚችሉ ጥልቀት እና ስፋት ያላቸው የታሪክ መዛግብት ወይም ሌሎች የስነ ፅሁፍ ስራዎች የተገኙ አይመስለኝም። የስልጣኔአቸውን ዘይቤ የተቃኘበት ፍልስፍናም ቢሆን በዚያን ጊዜ በነበረ የንግድ ትስስር ምክንያት ከግሪክ እና ከመካከለኛው ምስራቅ በተገኙ መፃህፍት የእውቀት ምንጭነት የተሸመነ ሊሆን እንደሚችል የሚጠቁሙ ወደ ግዕዝ ጭምር የተተረጎሙ መጻህፍት በማስረጃነት ሊቀርቡ ይችላሉ። የእነ ፕሌቶ እና አሪስቶትል መጻህፍቶች በቀደምት ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ዘንድ እንደሚታወቁ አንዳንድ የታሪክ ተመራማሪዎች ይገልፃሉ። የእነዚህን ታላላቅ ፈላስፎች ስራ ወደ ራስ ቁዋንቁዋ በመመለስም ሆነ የተፃፉበትን ቁዋንቁዋ በማጥናት መረዳት እና ጥቅም ላይ ለማዋል መሞከር በራሱ በዚያን ጊዜ የነበሩት ለቃውንት ምንኛ በፍልስፍና መዝገበ ቃላት ውስጥ ያሉትን ከበድ ያሉ ፅንሰሀሳቦችን ተዋህደዋቸው እንደነበሩ ፍንጭ ይሰጣሉ። ይሄም ሆኖ ግን የቀደምት ኢትዮጵያውያን ስልጣኔ አሻራዎች ሆነው የምናገኛቸውን የሀውልትና የስነ-ህንጻ ቅርሳቅርሶች፣ የእደ-ጥበብ ውጤቶች፣ ያሬዳዊ ዜማ (የሬዳዊ አስተምህሮ አላልኩም) ወዘተ፤ በዘያን ገዜ ከነበረው ፍልስፍናዊ አብርሆት ጋር ተዛማጅነት ይኑራቸው አይኑራቸው ሊያስረዳን የሚችል አንድም መዝገብ ከታሪክ ማህደር ማግኘት አልተቻለም። በዚህ ላይ አትናትዮሳዊው ክርስትና “በብህትውና እና ተአምራታዊነት” ሰበብ ቀደምት ሊቃውንቱ በህሊናቸው ጥረት ያስገኙአቸውን የስልጣኔ ሀብታት እድገታቸው እንዲገታ ከተቻለም እንዲጠፋ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ሚና ተጫውቶአል።

እዚህ ላይ “ታድያ እጉዋለ የትኛውን ኢትዮጵያዊ ስልጣኔ ነው ደመናውን ገልጦ ከምእራባዊው ስልጣኔ ጋር ሊያዋህድ የተነሳው?” የሚል ጥያቄ ማንሳቱ ተገቢ ነው።

“ስልጣኔ ማለት” ይላል ሊቁ “ መጀመሪያ ሰው በህሊናው ውስጥ ያሉትን ሀብታት መርምሮ ተረድቶ መሪነቱን ካወቀ በሁዋላ ዝቅተኛውን የስሜት ወይም የፍትወት ዓለም አርቆ ገርቶ ለህሊናው ያስገበረ እንደሆን ስልጣን ያለው እንደሆን የሚሰጠው ቅፅል ነው:: ሁለተኛ በዙሪያው ያሉትን ስነ ፍጥረቶች ለራሱ እንዲያገለግሉ ለማስገበር የሚያደርገው ጥረትና ከዚያም የሚገኘው ውጤት ስልጣኔ ይባላል::”

አትናትዮሳዊው ክርስትና ደግሞ “ሰው ነፃ ፈቃድ ብሎ ነገር የሌለው ጎስቁዋላ ፍጥረት ሲሆን፤ እጣፈንታው የሚወሰነውም በፈጣሪው ፀጋና ቸርነት እንጂ ምግባር በራሱ ወሳኝ ሚና የለውም” በሚለው አስተምህሮቱ የመጀመሪያውን ክፍል የስልጣኔ ትርጉም የባርነት ትርጉም እንዲይዝ አድርጎታል። ማለትም “በህሊናው ውስጥ ያሉትን ሀብታት መርምሮ ተረድቶ መሪነቱን ካወቀ በሁዋላ ዝቅተኛውን የስሜት ወይም የፍትወት ዓለም አርቆ ገርቶ ለህሊናው ያስገበረ እንደሆን ስልጣን ያለው እንደሆን” የሚለውን፤ ሰው ተቀባይ በመሆን ትእዛዛትን የሚያከብር እና በፆም፣ በፀሎት፣ በብህትውና ሆኖ የስጋ ፍላጎትን በመቅጣት አምላኩን እያገለገለ መኖር ያለበት ፍጡር አድርጎ ይወስደዋል። ሁለተኛውን ክፍል የስልጣኔ ትርጉምን ደግሞ የተአምራታዊነት ስብከትን በመትከል “በዙሪያው ያሉትን ስነ ፍጥረቶች ለራሱ እንዲያገለግሉ ለማስገበር የሚያደርገው ጥረትና ከዚያም የሚገኘው ውጤት” ተቁዋዳሽ እንዳይሆን አኮላሽው። ሁለተኛውን ክፍል የስልጣኔ ትርጉም ፍፁም የተኮላሸ እንዲሆን አድርጎት ይሄውና ከ1500 ዓመታት በላይ ቢዘልቅም፤ በመጀመሪያው ክፍል የስልጣኔ ትርጉም ግን ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት በየዘመናቱ የተለያዩ ዘዴዎችን በማፍለቅ አትናትዮሳዊውን ክርስትና በአልሞት ባይነት ሲፋለሙት ኖረዋል። ይሄን የመጀመሪያውን ክፍል የስልጣኔ ትርጉምን ይዞ የሚገኘውን መንፈስ ነው እንግዲህ ሊቁ እጉዋለ ከምእራባዊው ስልጣኔ ጋር ሊያዋህደው የተነሳው።

ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት በነፃ ፈቃዳቸው ላይ የተመሰረተ መንፈሳዊ ልእልናቸውን የሚጠብቁበት ዘዴ አስገኝተዋል ብዬ ከምወስደው አንዱ ቅኔን ነው። በዚህ ፅሁፍ አውድ ቅኔን የምተረጉመው ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የነፃ ፈቃዳቸው መገለጫ ማሳያ የሆነውን ፍልስፍናዊ ሙግታቸውን ኪነ-ጥበባዊ ውበትን አላብሰው፣

በጥቂት ስንኞች ቁዋጥረው ወይም በአእምሮአቸው ቆጥረው (ቅኔ ቆጠረ እንዲል) የሚገልጹትን ከፍታ ያለው ሃሳብ ነው። እጉዋለም ቅኔ ማለት “ምስጢር የተመላ የረቀቀ ፍልስፍና የተከማቸበት ማለት ነው” ይለዋል።

ስለዚህ አትናትዮሳዊ ክርስትና ደመና ሆኖ የሸፈነውን ጥንታዊውን የኢትዮጵያ ስልጣኔ መንፈስ ቁዋጠሮ (DNA) ተሸክመዋል ብዬ የማስባቸውን እና ለአንድ ሺህ ዓመታት ያክልም የክርስትናውን አስተምህሮ ሲገዳደሩ ለነበሩት ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት በነፃ ፈቃዳቸው ላይ የተመሰረተውን መንፈሳዊ ልዕልናቸውን ይገልፃሉ ያልኩዋቸውን ሶስት በጣም የታወቁ ፍልስፍናዊ ቅኔዎችን እንመለከታለን። እጉዋለ ከምእራባዊው ስልጣኔ ጋር ሊያዋህደው የሞከረውን የኢትዮጵያ የስልጣኔ ዘይቤንም ይበልጥ እንድንረዳው ያግዘናል።

1. **ባህቲቶ ነቢረ እግዚአብሔር ፈርሀ**
እም ኢሀልዎ ነዋም እስመ ዝ ዓለም አንቀሐ::

ብቻውን መኖር እግዚአብሔርን ቢያስፈራው
ካለ መኖር እንቅልፍ ይህንን ዓለም ሰራው:: ብሎ ገጣሚ ኤፍሬም ስዩም ተርጉሞታል

2. **ኮንኖ ሀጥአን ክርስቶስ ኢይደልወከ ምንተ**
አፍቅሩ ፀላእተክሙ እስመ ትብል አንተ ::

ክርስቶስ ሆይ አንተ ራስህ ጠላቶቻችሁን ውደዱ ብለህ አስተምረህ ሀጢአተኞችን ለምን ትኮንናለህ እንደማለት ነው።

3. **ሙሴ ፈጠረ ፈጣሪሁ**
ወፈጣሪ ፈጠረ ኪያሁ::

ሙሴን ፈጥሮታል የምንለው ፈጣሪ ሙሴ ራሱ ፈጥሮ የነገረንን ነው እንደማለት ነው።

እነዚህን ቅኔዎች ከደመና በታች ሆነን ብንተረጉማቸው፣ ስለ አምላኩ እግዚአብሔር በከንቱ የሚመራመር ከንቱ፤ ሀጢአት ብንሰራ ምናለበት የሚል የሰነፍ ሰው ሃሳብ፤ ጭራሽ ደግሞ እግዚአብሔር የለም የሚል ከሀዲ፤ ወዘተ ወዘተ እያልን መተርጎም እንችላለን:: ነገር ግን በቅን ህሊና ሆነን ብንመራመርባቸው የጥንታዊው ስልጣኔ መንፈስ የተገነባባቸው የመሰረት ዲንጋዮች ሆነው እናገኛቸዋለን::

እዚህ ላይ ከቀደምት ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት መካከል በግልፅ እግዘአብሄር-የለሽ (Atheist) ነኝ ባይ በግሌ አላውቅም። ነገር ግን በአትናትዮሳዊው ክርስትና ተውጠው ይሄንን ዓለም የሚያናንቁ እና አመክንዮአቸውን የሚጥሉና የሚያንቁዋሸሹ ተቀባዮች አይደሉም። ለነዚህ ሊቃውንት በእውቀት ላይ ያልተመሰረተ ሀይማኖት ትርጉም የለውም።

ከላይ የጠቀስኩዋቸው ቅኔዎች ባለቤቶቻቸው በህይወታቸው ውስጥ በተግባር ቢኖሩበትም ባይኖሩበትም ለቅኔዎቹ እኔ ከምሰጣቸው ትርጉዋሜ አንፃር የባለ ቅኔዎቹ ህይወት ፋይዳ የለውም። የነዚህ ቅኔዎች መንፈስ ግን በግለሰብ ነፍስ ውስጥ ጎልቶ የሚታይ የነፃነት መንፈስ ነው። የነፃነት መንፈስ ደግሞ በግለሰብ ነፍሰ ልዕለ-ሰብእና (self-esteem) ላይ ይመረኮዛል። የግለሰብ ነፍስ ልእለ-ሰብእና የሚገለፀው ደግሞ በዶስቶየቭስኪ የክርስቶስ ትምህርት ትንታኔ መሰረት በሶስት ነገሮች ይገለፃል። 1ኛ ሁሌም ነፃነትን ማስቀደምና ምስጢርን አለመቀበል (በእንጀራ ብቻ አለመኖር)፣ 2ኛተአምራታዊነት (Mysticism) አለመቀበል፣ እና 3ኛ በነፍስ ፈቃድ ላይ ሌላ የበላይ አካል (Authority) አለመቀበል። (በዚህ ዙሪያ ከዚህ በፊት በፌቡ ገፄ ላይ “ሰው አምላክ መሆንን ሻተ ተሳካለትም” በሚል አብራርቻለሁ።)

ቀደምት ኢትዮጵያውያን ሊቃውንትም ይኼን ክርስቶስ ያስተማረውን ፍፁም የበላይ የሌለው የነፃ ፈቃድ ትምህርት በሚገባ እንደተረዱት በነዚህ ቅኔዎች መነፅር መረዳት ይቻላል።

ወደ ቅኔዎቹ ስንመለስ፣ የእነዚህን ቅኔዎች መንፈስ የተላበሱ ሊቃውንት ሦስቱን ፈተናዎች (ተአምር፣ ምስጢር እና ስልጣን) አያንበረክኩዋቸውም ተሻግሮዋቸዋል:: ተአምር አያጉዋጉዋቸውም፤ አለ ብለው የሚቀበሉም አይመስሉም:: ምርምር ግን ያነቃቃቸዋል:: በመሰረቱ ሰው ተአምር የሚያስፈልገው እግዚአብሔርነት በውስጡ የለም ብሎ ከተቀበለ ብቻ ነው:: ቅዱስ አትናቴዎስ የተባለ ግብፃዊ (አርዮስን ተከራክሮ የረታ፣የመጀመሪያውን ጳጳስ አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሀንን ሾሞ ወደ ኢትዮጵያ የላከው አባት ነው:: አትናትዮሳዊ ክርስትና ያልኩትም በሱ ምክንያት

ነው።) የሰው ነፍስ እንደ ማንኛውም ፍጥረት እምሃበ አልቦ (from nothing) ነው የተፈጠረችው ይላል። ስለዚህ በሰው እና በእግዚአብሔር መካከል የግኙኝነት ድልድይ የሌለው (unbridgeable) ትልቅ ሸለቆ አለ። እንዳው እግዚአብሔር ራርቶለት በቸርነቱ ፀጋውን እፍፍ ብሎ ካልሰጠው በስተቀር፤ ሰውማ ፈጣሪውን ሊያውቅ ቀርቶ ክፉውን ከደግ መለየት እንኩዋን የማይችል ረዳትየለሽ (helpless) ፍጡር ነው ይላል። እንደዚህ አይነት ትምህርት ለተቀበለ ሰው ነው ተአምር የሚያስፈልገው።

ኦሪገን (አትናቴዎስ ወጣት እያለ የዚህ አባት ተከታይ ነበር በሁዋላ እርግፍ አድርጎ ቢተወውም) የተባለ ደግሞ የሰው ነፍስ ከራሱ ከእግዚአብሔር የተገኘች የእስትንፋሱ እፍታ ናት። ስለዚህ ሰው በነፍሱ መስተዋትነት አማካኝነት እግዚአብሔርን ማወቅም ማየትም ይችላል። አዋቂ ነፍስ ስለሆነች ያለችው ክፉና ደጉንም ለይቶ ማወቅ ይችላል ይላል። ምንም እንኩዋን ይህ ቅዱስ በኦሪየንታል አብያተክርስቲያናት ዘንድ የተገለለ ቢሆንም፣ የኛ ቀደምት ሊቃውንት ግን ከኦሪገን ጋር የሚሰማሙ ይመስላል። በዚህ እይታ መሰረት የእግዚአብሔር ፍንጣቂ የሆነችውን ነፍስ የያዘን ሰው ፀጋ ያስፈልገዋል ማለት የእግዚአብሔር ፍንጣቂ የሚለውን ሀሳብ (concept) በትክክል አለመረዳት ይመስላል። ፀጋስ ምንድነው? የሚል ጥያቄ ያስነሳል። አይደለም የእግዚአብሔር ፍንጣቂ የትንሽየዋ አተም የኒኩለስ ፍንጠቂ እንኩዋን ሃይሉ እጅግ የበዛ ነው። ምናልባት ፕሌቶ እንደሚለው የሰው ነፍስ በስጋው እስርቤት ውስጥ ስላለች በሚል እንኩዋ ክርክር ቢነሳ፤ ክርስቶስ ራሱ ተፈትኖ፣ የሰጋን ፈቃድ ለነፍስ ማስገዛት እንደምንችል በተግባር አሳይቶናል ብለው የሚከራከሩ ሊቃውንት ናቸው።

ተአምር እና ምስጢር ተመሳሳይነት ስላላቸው እነዚህ ታላላቅ ሊቃውንት ምስጢር የሚያጉዋጉዋቸው ሊፈለቅቁት ሲፈልጉ ብቻ ነው ብየ አልፈዋለሁ።

ሌላው ስልጣን ነው። ልዕለ ሰብእና (self esteem) ያለው ሰው ሌላ ሰው እንዲንበረከክለትም አይፈቅድም እሱም ለሌላ መንበርከክን አይቀበልም። ስልጣን እንዲኖረው የሚፈልገው በራሱ ላይ ብቻ ነው። ማለትም እጉዋለ እንዳለው “በህሊናው ውስጥ ያሉትን ሃብታት መርምሮ ተረድቶ መሪነቱን ካወቀ በሁዋላ፣ ዝቅተኛውን የስሜት ወይም የፍትወት ዓለም አርቆ ገርቶ ለህሊናው ያስገበረ እንደሆን፣ በራሱ ላይ ስልጣን ያለው እንደሆን ነው።” ስለዚህ የስልጣኔ ቁልፍ መንገድ በራስ ላይ መሰልጠን ነው ማለት ነው።

አሁን ሦስቱ ፍልስፍናዊ ቅኔዎች እንዴት ከጥንታዊው ስልጣኔ ጀርባ ያለውን ሀሳብ እንደሚገልፁ በአጭሩ ላብራራ። አንድ ሰው ትላልቅ ፈጠራዎችን ለዓለም ማበርከት የሚችለው በመጀመሪያ ሦስት ደረጃዎችን (stages) ማለፍ ከቻለ ነው እላለሁ። ቅኔዎቹ እነዚህን ደረጃዎች የሚያሳዩ ስለሆኑ በያንዳንዱ ደረጃ ውስጥ በምሳሌነት አሰቀምጬአቸዋለሁ።

1. **ብዥታ (Confusion) ማስወገድ:-** ሰው በህሊናው ውስጥ ያለውን የእውቀት ክምችት በእጉዋለ አባባል “እንደ የድሮ ቆሎ ተማሪ አኮፋዳ ውስጥ ያለ እህል” የተደበላለቀ ከሆነ የተስተካከለ ሀሳብ ሊኖረው አይችልም። የተስተካከለ ሀሳብ ከሌለው ደግሞ ሊደናገር ከሆነ እንጂ ሊፈጥር አይችልም። ስለዚህ የተዘበራረቁ ሀሳቦችን በስርዓት አስተካክሎ አቀናጅቶ በማስቀመጥ የራስ ሊባል የሚችል መደምደምያ ላይ መድረስ በፈጠራ ሂደት ውስጥ ተቀዳሚ ስራ መሆን አለበት።

ቀደምት ሊቃውንት አባቶቻችን መጀመሪያ ራሳቸውን ከብዥታ ማፅዳት ተቀዳሚ ስራቸው እንደነበረ የሚያሳየን 3ኛው ቅኔ ነው። እኔ ሳስበው ይህ ባለ ቅኔ በሙሴ መፃህፍት ደስተኛ መሆን አልቻለም። አንዳንድ የመፅሀፍ ቅዱስ ታሪክ አዋቂዎች እንደሚሉትም (እኔም እንደማምነው) በሙሴ መፃህፍት ውስጥ ሌሎች ሰዎች የራሳቸው ሃሳብ ሁሉ ጨምረውበታል። ስለዚህ ባለ ቅኔው ፣ባጠቃላይ በሙሴ መፅሀፍ ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔር ስዕል ስላልተቀበለው፣ ይሄ አንተ የፈጠርከው እግዚአብሔር ነው ሲል፡ “ሙሴ ፈጠረ ፈጣሪሁ” አለ። በሙሴ መፅሀፍ ውስጥ እግዚአብሔር ሰውን እንደፈጠረ ስለሚናገር ደግሞ፣ ሙሴም ሰው ስለሆነ፡ “ወፈጣሪ ፈጠረ ኪያሁ” አለ። ከብዥታ ወጥቶ የተስተካከለ ሀሳብ ይዞ የራስ መደምደምያ ላይ ሲደርሱ እንዲህ ያለ ያማረ ቅኔ ይወጣዋል።

2. **የቆየ የነበረን እውቀት በድፍረት መተቸት መቻል:-** የተስተካከለ ሀሳብ ይዘን የራሳችን መደምደምያ ላይ ከደረስን በሁዋላ፤ ያለ የነበረ እውቀትን መተቸት ስንችል፣ ያለውን ክፍተት ወይም ደግሞ ስህተት አይተን መፍትሔ ሀሳብ እንድንፈልግ ይረዳናል።

ሊቃውንቱ ስህተት ካዩ ከመተቸት ወደሁዋላ እንደማይሉ (ከቤተ ክርስቲያን ጭምር እንኩዋን የሚያጣላቸው ቢሆን) የሚያሳየን ደግሞ 2ኛው ቅኔ ነው:: ይህ ባለ ቅኔ ደግሞ ሀጢአት ብንሰራ ምናለበት ለማለት ፈልጎ ሳይሆን ሰው ስራውን እንዳይሰራ እና በህሊናው እንዳይመራ በትኮነናታለህ ፣ገሀነም ትገባታለህ! ሰበብ በፍርሀት ጠፍርጎ ለመያዝ የሚደረጉትን ነገሮች ለመቃወም ይመስለኛል:: በሌላ በኩል ደግሞ የክርስቶስን ትምህርት ሰውን በፍቅር መሳብ ስለሆነ፣ "የማስፈራራት ትምህርት ከወዴት መጣ? ክርስቶስ ግን እንዲህ አይነት ነገር አያስፈልገውም፤ ብሎ ቤተ ክርስቲያንን እና አትናቲዮሳዊው ክርስትናን ሲተች ነው::

3. **ፈጠራ:-** እንግዲህ አንድ ሰው የተስተካከለ ሀሳብ ካለው፣ ስህተትን ለይቶ አውጥቶ በቅን ህሊና መተቸት የሚችልበት ደረጃ ላይ የደረሰ ከሆነ ነፃ ሰው ነው:: በነፃ ፈቃዱ ነው የሚመራው:: የሚቀረው አዲስ ነገር መፍጠር መፈልሰፍ ነው:: አዲስ ነገር ለመፍጠር የሚተጋ ሰው ግን ሀሳቡን የሚጋራው ሰው ለማግኘት ከባድ ስለሆነ፣ ብዙውን ጊዜ ብቸኛ ነው:: ፈጠራው አካላዊ ቅርፅ ይዞ እስኪወጣ ድረስም በሀሳብ ምጥ እረፍት የለውም:: በአንድ ወቅት ሊቁ ዶክተር ዕጉዋለ “ፈጠራ እና ፈጣሪ የሚሉ ሀሳቦች ቢያያዙ ደስ ይለኛል” ብሎ ነበር 1ኛው ቅኔ የሚገልጠው ይኼንን ነው:-

ባህቲቶ ነቢረ እግዚአብሔር ፈርሀ
እም ኢሀልዎ ነዋም እስመ ዝ ዓለም አንቀሀ::

የነዚህ ሦስት ቅኔዎች ሀሳብ ጥንታዊ ስልጣኔአችን የተገነባበት መሰረት ዲንጋይ ሆኖ ነበር :: ምን ይታወቃል

“አማን በአማን አማን በአማን
ይመጣ ይሆናል የተሻለ ቀን”

እንዳለው እጉዋለ ገብረዮሀንስ፣ የተሻለ ቀን እንዲመጣ ተስፋ በማድረግ በሚቀጥለው ክፍል ደግሞ የበተዋህዶ ከበረን ፕሮጀክት ሂሳዊ ምልከታ አቀርባለሁ።

ሰላም

እጉዋለ

#Eguale

#እጓለ

በምስራቅ አፍሪካ ዳርቻ ሰማይ ላይ (ክፍል 2)

በመጀመሪያው ክፍል ላይ የጥንታዊውን የኢትዮጵያ ስልጣኔ መንፈስን ዳስሰናል። በዚህ ክፍል ደግሞ በተዋህዶ ከበረ ፕሮጀክት ላይ ሂሳዊ ምልከታ (Critique) አቀርባለሁ።

የ በተዋህዶ ከበረ ምንነት

የበተወህዶ ከበረ ፕሮጀክት ሀሳብ፣ ሰው አምላክ ሆነ አምላክ ሰው ሆነ... የሚለውን ኦርቶዶክሳዊ ትምህርት አዙሮ፣ ሰውን ማዕከል (Anthropocentric) ያደረገውን ምዕራባዊው ስልጣኔ እና አምላክን ማዕከል (Theocentric) ያደረገውን ምስራቀዊ (ኢትዮጵያዊ) ስልጣኔ በማውሃድ በኢትዮጵያ ጥንታዊ የስልጣኔ ጉዞ ውስጥ በፅሁፍ ተብራርቶ ባይገለፅም በተግባር ጎልቶ ይታይ የነበረውን ማህበራዊ ፍልስፍናን “በተዋህዶ ከበረ” በሚል ስያሜ አጥምቆ በ20ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ ሂወት ሊዘራበት ተነሳስቶ የነበረው ኢትዮያዊው ኮከብ ብርቅየው ፈላስፋ እጉዋለ ያፈለቀውን ሀሳብ ለማመልከት ነው ።

ለመሆኑ እነዚህ ሁለት ፍልስፍናዎች (የኑሮ የስልጣኔ ዘይቤዎች) ማዋሐድ ይቻላልን?

እጉዋለ በ የከፍተኛ ትምህርት ዘይቤ መጽሀፉ ላይ ሁለት የተለያዩ የተዋህዶ ሃሳቦችን አንድ ላይ አጭቆ ነው የሚያቀርባቸው። ሁለት መሰረታዊ (Fundamental) ልዩነት ያላቸውን ፍልስፍናዎችን (ስልጣኔዎችን) ለማውሀድ የሚሞክርበት ሀሳብ እና፤ ሁለት ዘመዳሞች የሆኑ ፍልስፍናዎችን (ስልጣኔዎችን) ለማውሀድ የሚሞክርበት ሀሳብ። ከዚህ የተነሳ ይሄንን መፅሃፍ ያነበቡ ሰዎች ሁለት የተለያዩ መደምደምያ ላይ ደርሰው ሲወጡ እናስተውላለን።

እኔ ባለኝ ተሞክሮ አብዛኞቹ ፣”እጉዋለ ለማውሀድ የሞከረው ድህረ አክሱም የተዋወቅነውን በአትናትዮሳዊ ክርስተና የተቃኘውን የኑሮ ዘይቤ ወይም ስልጣኔ እና ምእራባዊውን የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ስልጣኔን ነው” ይላሉ። እጉዋለ እንዴትና በምን መንገድ እንዲዋሀዱ እንደፈለገ ሲገልፁም እጉዋለን ጠቅሰው እንዲህ ይላሉ፣ “በተፈጥሮ ዘይትነት ያለው ዛፍ አለ። ፍሬ ማፍራት ስለ ተሳነው ቅርንጫፎቹን ይቆረጡአቸዋል። በነሱ ፈንታ አውልዓ ገዳም የምድረበዳ ዛፍ በዘይቱ ግንድ ላይ ተቀጥሎ እንዲያድግ ይተክላሉ። ተቀፅላው የስሩ ህይወት ተካፋይ ስለሚሆን ዘይትነትንም ያገኛል። ግን ፈርቶ መኖር አለበት። በቅርንጫፍነቱ መኩራት አይገባውም። ምክንያቱም ስር ቅርንጫፍን ይሸከማል እንጂ ቅርንጫፍ ስርን አይሸከምም። ይህ በጣም ረቂቅና ደግሞም ጉልህ የሆነ ምሳሌ ለተጠቀሰው ችግር [ሁለቱ ስልጣኔዎች ማለትም የኢትዮጵያ እና የምእራብ እንዴት ይወሀዱ] የታመነ መፍትሄ ነው። ለእኛ የተፈጥሮ ዘይትነት ያለው ዛፍ የሀገራችን ስልጣኔ ነው። ተቀፅላው በሱ ላይ ተጣብቆ የስሩ የዘይቱ ተካፋይ መሆን አለበት። ብቻውን ቢቆም አውልዓ ገዳም፣ ወፍ አባቱ፣ የምድረ በዳ ቅጠል ሆኖ ይቀራል። ከኢትዮጵያ ሊቃውንት “እለ እምፍጥረቶሙ ዘይት” ከሚገኘው እውቀት ጋር አዲሱ ከምእራብ የሚመጣው የሃሳብ ዘዴ ሲፃመር ሲዋሐድ የእውቀት ዛፍ ይለመልማል ሲያዩት እንኩዋን ለዓይን ያስደስታል።”

እኔ ደግሞ እላለሁ ይሄ ትክክለኛውን የተዋህዶ ሀሳበ ሳይሆን የሚገልጸው በቃ ተቀፅላን ነው። እጉዋለ በፈላስፋነቱ አምላክን ማዕከል (Theocentric) ያደረገ ፍልስፍና እና ሰውን ማዕከል (Anthropocentric) ያደረገ ፍልስፍና ማዋሐድ እንደማይቻል በፍልስፍና እና በሀይማኖት ታሪክ ተሞክሮ የከሸፈ ዘዴ እንደሆነ በደንብ ይገነዘባል ብየ አስባለሁ።

በ 13ኛው ክዘ የነበረ ቶማስ አኩዋይናስ የተባለ ካቶሊካዊ ፈላስፋ፣ የፈጣሪ እና የእምነት (Faith) ፀሮች ተብለው ተፈርጀው የነበሩትን አመክንዮ(Reason) እና ሎጂክ፣ "ሰው በእውቀት ታግዞ እግዚአብሔርን ማወቅ የሚችልባቸው መንገዶች ናቸው" ብሎ ከፍታ ቦታ ላይ እንዲቀመጡ ሞግቶአል። ለቶማስ አኩዋይናስ ፍልስፍናን ለመረጡ ሰዎች አምክንዮአቸው ከእግዚአብሄር ጋር የሚገናኙበት ድልድይ ሲሆን፤ ፍልስፍናን ላልመረጡ ወይም ደግሞ መፈላሰፍ ለማይችሉ ደግሞ በእምነታቸው (Faith) እግዚአብሔር ይገለጥላቸዋል። ስለዚህ አመክንዮ (Reason) እና እምነት (Faith) ወደ አንድ መዳረሻ የሚወስዱን የተለያዩ መንገዶች እንጂ አንዱ በሌላኛው ላይ መሰልጠን እንደማይችል ነው አኩዋይናስ የሚያብራራው ። እንዲያውም፣ ምንም እንኩዋ አኩዋይናስ የአሪስቶትል

ፍልስፍና ወደ እግዚአብሔር የሚያደርስ የፍልስፍና መንገድ እንደሆነ ቢቀበልም፤ የክርስትናን መሰረተ ትምህርት በአሪስቶትል መሰረት ላይ መትከልም ሆነ የአሪስቶትልን ፍልስፍና በክርስትና መሰረት ላይ መትከልን ፈፅሞ አይቀበለም። እጉዋለም ይሄን የቶማስ አኩዋይናስ መከራከሪያ ሀሳብ ከፍልስፍና ትምህርቱ አብጠርጥሮ እንደሚያውቀው ጥርጣሬ የለኝም።

ከዚህ በተጨማሪ የኦትናትዮሳዊው ክርስትና አቀንቃኝ ከሆኑት ኢትዮጵያውያን ምሁራን አንዱ የሆኑት አባ ጎርጎርዮስ፣ የቤተ ክርስትያን ታሪክ በሚል መጽሀፋቸው ላይ የክርስትና እና የፍልስፍና ፍፀም አለመጣጣም፣ ታሪክን አጣቅሰው እንዲህ በማለት ገልፀውታል፦

“በመሰረቱ ፍልስፍና እና ክርስትና በታሪክም ሆነ በዓላማ ምንም ግኙኝነት የላቸውም። ፍልስፍና ማለት አንድ ሽፍን ነገር ፈልፍሎ ለማየት አይቶም ለማወቅ የሚረዳ የአዕምሮ መሳሪያ መፅሔት ማለት ነው። ወይም የተደበቀን ምስጢር ፈልፍሎ የሚያወጣ የአእምሮ መንጠቆ ማለት ነው።” ይሉና ትንሽ ወረድ ብለው ደግሞ “የፍልስፍና ዋናው ጉድለት በስነ ፈጥረት ጀምሮ በስነ ፍጥረት መጨረሱ ነው፤ ክርስትና ግን በሰው አእምሮ ከመታሰብ በላይ የሆነ የእግዚአብሔር ጥበብ ነው። ... በክርስትና መሰረተ ትምህረት ውስጥ የማእዘኑን ራስ የያዘው ይህ የአምላክ መገለጥ በተአምራት ስለሆነ በስነ ፍጥረት ህግና በፍልስፍና የምርምር ስርዓት ይሆናል ተብሎ የማየታሰብ ነው” ይላሉ። ምንም እንኩዋ አባ ጎርጎርዮስ አእምሮ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው ብለው ስለሚያምኑ፣ ሰው በአእምሮው ቢመራመር ክፋት እንደሌለው ቢገልፁም ቅሉ፤ ፍልስፍናና ክርስትና ግን ፈፅመው መዛመድ እንደማይገባቸው አበክረው ሰያስታውሱን እንዲህ በማለት ነው፣ “ ክርስትና ይመረምራል ይተረጉማል፤ ግን ትርጉዋሜውም ሆነ ምርምሩ የእግዚአብሔርን ተአምራት ጨብጦ እንጂ የስነ ፍጥረትን ህግና የሰውን ጠባብ አእምሮ ተመርኩዞ አይደለም፤ ማለትም በእግዚአብሔር ጀምሮ በእግዚአብሔር ይጨርሳል ። ሁለቱ ማለትም ፍልስፍና እና ክርስትና ምንም ቢሆን የማይዛመዱ ናቸው።”

ይሄ የአባ ጎርጎሪዮስ ሃሰብ፣ እጉዋለ ተቀጽላ ብሎ ፍልስፍና የበታች፣ እምነት የበላይ አድርጎ ከገለጸው ሃሳብ ጋር ይስማማል እንዳንል እንኩዋ፤ “ፍልስፍና እና ክርስትና በታሪክም በዓላማም ግኙኝነት የላቸውም” የሚለውን ሀሳባቸውን ስናስታውስ እንደማይስማሙ እናስተውላለን። ማለትም በክርስትና ትምህርት የሰው ዓላማ መሆን ያለበት የእግዚአብሔርን ክብር በወዲያኛው ዓለም መውረስ ስለሆነ፤ እዚህ ምድር ላይ በጊዚያዊነት ሲመላለስ ለእለት ጉርሱ፣ ለቀን ልብሱ ለሚሆነው ነገር በመራመር ቢያገኝ ክፋት የለውም ቢባል ነው እንጂ የሚያመረው፤ የተራቀቀ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ምርምር ላይ ስለምንስ አምላኩን የሚያገለግልበትና የሚገዛበት ጊዜውን በከንቱ ያጠፋል? አባ ጎርጎሪዮስ ጥሩ አድርገው እንደገለፁት “ በክርስትና መሰረተ ትምህረት ውስጥ የማእዘኑን ራስ የያዘው ይህ የአምላክ መገለጥ በተአምራት ስለሆነ በስነ ፍጥረት ህግና በፍልስፍና የምርምር ስርዓት” የት ለመድረስ ነው የተራቀቀውን የሳይንስና የቴክኖሎጂ ምርምሮችና ስርፀቶችን በክርስትናው ላይ በተቀፅላ ሊተክል የሚጣጣረው?

ታዲያ ይሄንን መከራከሪያ ሃሳብ በምን ሙግት አልፎት ነው እምነት የበላይ፣ አመክንዮ የበታች የሆኑበት የተቀፅላ ሀሳብ ያመጣው? ብዬ ለራሴ ስጠይቅ ማግኘት የቻልኩት መልስ የሚከተለውን ነው።

እጉዋለ አነደዚህ ዓይነት የተቀፅላ ሃሳብ ሊያመጣ የተገደደው፣ እጉዋለ የበተዋህዶ ከበረን ሀሳብ ይዞ ብቅ ባለበት በ1950ዎቹ ጊዚያት የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ከምእራቡ የኑሮ ዘይቤ እና የዚሁ የምእራቡ ዓለም ፍልስፍና ውጤቶች የሆኑትን ሳይንስና ቴክኖሎጂን ለማስተዋወቅና ለማላመድ እጅግ አስቸጋሪ ስለነበረ፣ ይዞት የመጣውን ትክክለኛ የበተዋህዶ ከበረ ሃሳብ ለሰሚ ጆሮ ከባድ እንዳይሆን ሰግቶ ቀስ በቀስ እያለዘበ ለማቅረብ አስቦ የነበረ ሊሆን ይችላል ብዬ እገምታለሁ።

ለዚህም እጉዋለ በዋናነት ፈላስፋ ቢሆንም የከፍተኛ ትምህርት ዘይቤን የፃፈው ግን እንደ ጋዜጠኛ ሆኖ ነው። አብዘኞቹ የመጽሀፉ መጣጥፎች በዚያን ጊዜ እጉዋለ ይጠቀምበት በነበረ “መምህር አብራራው” በሚል ስያሜ የሚታወቅ የሬድዮ ፕሮግራም ላይ የቀረቡ መሆናቸውን ከህይወት ታሪኩ መረዳት ችያለሁ። እዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን እንደጋዜጠኛ ሆኖ ሲቀርብ በፍልስፍና ቅኝት ውስጥ ሆኖ መሆኑን መዘንጋት እንደሌለብን ነው።

እጉዋለን እንደ ጋዜጠኛ ሆኖ ሲቀርብ ትኩረቱ ሁለቱ ስልጣኔዎች ማለትም የኢትዮጵያ እና የምእራቡ ላይ ሲሆን፤ እንደ ፈላስፋ ግን "ሃሳብ" ላይ ያተኩራል። እንደ ጋዜጠኛ፣ ለዘመናት የቆየውን በኦትናትዮሳዊ ክርስትና የተቃኘውን የኢትዮጵያ ማህበረሰባዊ ፍልስፍና ወይም የኦኩዋኩዋር ዘይቤን ሊፈትነው ወይም ሊገዳደረው አይደፍርም። ይልቅ

አብዛኞቹ ጋዜጠኞች እንደሚያደርጉት ያለ በቂ መከራከሪያ ሀሳብ የቆየውን የኑሮ ዘይቤ እንደ መሰረት ወስዶ ጎድሎታል ያለውን ነገር ደግሞ እላዩ ላይ ሊጨምርበት ነው የሚሞክረው።

እጉዋለ አንደፈላስፋ ሆኖ ሲቀርብ ግን በዓለም ላይ የሚታወቁትን የፍልስፍና ፕሮብሌሞችን ለመመለስ የሚተጋ ሆኖ እናገኘዋለን። ችግሩ መፍትሄ ለመስጠት የሚሞክረው ፍልስፍናዊ ሰፊ-ንግግር (Discourse) መንገድ ተጠቅሞ ሳይሆን የጋዜጠኝነትን ሰባኪ አካሄድን ተከትሎ ነው። ይህ መንገድ የመረጠበት ዋናው ምክንያትም ሀሳቦቹ ለብዙሀኑ የሬድዮ እና የጋዜጣ ተከታታዮቹ ተደራሽ እንዲሆኑለት በማሰብ እንጂ ሙያዊ የሆነው የፍልስፍና አካሄድ ስለአቃተው እንዳልሆነ መገመት አይከብድም። ራሱም በመፅሀፉ መግቢያ ላይ እንዲህ በማለት ነግሮናል፡-

“አንባቢ እንደሚረዳው በዚህ ፅሁፍ የቀረቡት ሀሳቦች በራዲዮ ንግግር መልክ ለብዙ አድማጮች የህሊና ችሎታ እንዲስማሙ ሆነው የተዘጋጁ ናቸው። ... እንደምኞታችን ቢሆን በዚሁ አርእስት ማናቸውንም የመፅሀፍ አፃፃፍ ስነ ስርዓት በመከተል ደንበኛ ሰፋ ያለ ጥናት ባዘጋጀን ነበር። አሁንም አይቀረም። ከሌሎች የመንፈስ ችግሮች ጋር ለመታገል የግል ጥናታችንን ለመቀጠል ስላሰብን ለጊዜው ይህንን መፅሀፍ ያለ አንዳች ለውጥ ወይም መሻሻል እንዲታተም ተውነው። በሌላ ጊዜ እንመለስበታለን።”

እዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባን ጉዳይ፣ እጉዋለ እንደ ጋዜጠኛ ሆኖ ሲቀርብ ለዘመናት የቆየውን በአትናትዮሳዊ ክርስትና የተቃኘውን እና በኢትዮጵያ ኦርቶደክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ጫና ውስጥ ያለውን ማህበረሰባዊ የኑሮ ዘይቤ ፊትለፊት ሊጋፈጠው ሊገዳደረው (Challenge ሊያደርገው) ስላልቻለ ምናልባትም ስለተልፈሰፈሰ፤ ሊያዋህዳቸው የፈለጋቸው ስልጣኔዎች ይሄን በኦርቶዶክሳዊ ጫና ውስጥ ያለውን የኑሮ ዘይቤ እና የምእራቡ አለም የኑሮ ዘይቤ (ስልጣኔ) ሊመስል ይችላል።ግን አይደለም። ሆኖም ግን እጉዋለም ራሱ በኑሮው እና በፅሁፎቹ ለኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ባሳየው የተለሳለሰ አቋዋም እንዲህ እንዲተረጎምበት አስተዋፅኦ አበርክቶአል። ለዚህም ዋጋ ከፍሎበታል። ድንቅ የሆነውን የበተዋህዶ ከበረ ሃሳቡ ማንም ከቁብ ሳይቆጥረው ወይም ደግሞ ትክክለኛ ትርጉሙ ሳይተነተን እንደተዳፈነ ይሄው ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ አስቆጠረ።

እኔ ደግሞ እላለሁ፣ ፈላስፋው እጉዋለ ከምእራባዊው ስልጣኔ ጋር እንዲዋሀድ የፈለገው ትክክለኛው ኢትዮጵያዊ ስልጣኔ፣ በመጀመሪያው ክፍል ለመዳሰስ የሞከርኩትን ቅድመ አትናትዮሳዊ ክርስትና የነበረውን አክሱማዊ ስልጣኔ መሆን ሲገባው፤ እሱ ግን ከኦርቶዶክሳዊው አጎብዳኝነት ራሱን ነፃ ማውጣት ባለመቻሉ ጥንታዊውን የቀደምት አትዮጵያውያን ስልጣኔ የሆነውን አክሱማዊውን መንፈስ "ያሬዳዊ ስልጣኔ" የሚል አሻሚ ሀረግን መጠቀም መረጠ። ይሄን ለማድረግ የተገደደበት ምክንያት የሚመስለኝ፣ ምንም እንኩዋ ያሬድን በዜማ ፈጣሪነቱ እያወደሰ ሰማይ ሰቅሎ የቅድመ አትናትዮሳዊ ክርስትና አክሱም መንፈስ መገለጫ ተምሳሌት ሆኖ እንዲቀርብ ቢያደርግም፤ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ያሬድን ከዜማ ፈጣሪነቱ ይልቅ በ ብሩህ ዓለምነህ አገላለፅ "የሰሞነ ህማማት" አቀንቃኝነቱን አክብራ ቅዱስ እንደምትለው ስለሚያውቅ፤ ቅድመ አትናትዮሳዊ ክርስትና የነበረውን አክሱማዊ ስልጣኔ በያሬድ ለውሶ ማቅረቡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ምንጊዜም ሁነኛ መገለጫ ከሆነው የውግዘት እና የማሳደድ ችግር ያድነኛል ብሎ ሊሆን ይችላል።

አሁን ሂሳዊ ምልከታዬን እዚህ ላይ ይብቃኝና፣ “ለመሆኑ ቅድመ አትናትዮሳዊ ክርስትና የነበረው አክሱማዊ ስልጣኔ እና ምእራባዊው ስልጣኔ የሚዋሀዱበት መንገድስ በእጉዋለ መፅሀፍ ውስጥ ተብራርቶአል?” የሚል ጥያቄ መነሳት አለበት። መልሱም እንዴታ በሚገባ ነው። እንዲያውም ፈላስፋው እጉዋለ የበተዋህዶ ከበረ ሃሳብ እንዲያፈልቅ ገፊ ምክንያት የሆነው፣ “የስልጣኔ ሀብታት ከሰው ህሊና ጥረት የሚገኙ ስለሆኑ በየትም ቢወለዱ ዘመዳሞች ናቸው” የሚል ታላቅ ድንቅ ሃሳብ በመያዙ ነው እላለሁ።

በሚቀጥለው ክፍል የኔ የቤት ስራ አድርጌ የምወስደው ጋዜጠኛውን እና ቄሱን እጉዋለ ከበተዋህዶ ከበረ መንፈስ ሙሉ በሙሉ በማስወገድ፤ የፈላስፋውን እጉዋለ ፍለጋ ተከትዬ በተዋህዶ ከበረ ፕሮጀክት ምሉእነትን እንዲጎናጸፍ የእጉዋለን ሀሳቦች ማቃናትን ይሆናል። ቢያንስ ያልተበረዘውን የበተዋህዶ ከበረ ቅርፀ-አካልን(Anatomy) አስቀምጣለሁ ብዬ አምናለሁ።

ሰላም

በምስራቅ አፍሪካ ዳርቻ ሰማይ ላይ (ክፍል3)

"በአሜሪካ ጥላ ስር ያሉት የምዕራቡ ዓለም ሥልጣኔ እሴቶች እንዲወድሙ ሆነዋል። እነዚህ ሰለ ነፃነት፣ ሰብአዊ መብት፣ እና ሰብአዊነት(Humanity) የሚናገሩት ድንቅ ተምሳሌታዊ ማማዎች እንዲወድሙ ሆነዋል። እንደ ጭስ ነው የበነኑት።" አሳማ ቢንላደን

ይህ በተለምዶ 9/11 እየተባለ የሚጠራውን አሜሪካ ላይ የተደረገ የሽብር ጥቃት ከተከናወነ በሁዋላ ቢንላደን የተናገረው ነው ተብሎ በብዙ ሚዲያዎች ሲሰራጭ የነበረ ነው። እዚህ ላይ ቢንላደን እንዲህ ብሎ ተናግሮም ይሁን አይሁን፣ ንግግሩ አንድ ግልጽ የሆነ የማይካድ ሃቅ በውስጡ ቁዋጥሮአል- በዚህ ምድር ጫፍ የረገጠ የምዕራቡ ዓለም፣ በተለይም ደግሞ የአሜሪካ፣ እሴቶች ጥላቻ የት ደረጃ እንደደረሰ ወይም ሊደርስ እንደሚችል አመላካች ነው። ለመሆኑ አንድ ሰው "ነፃነትን" እና "ሰብአዊ መብትን" እስኪያንገሸግሹት ድረስ እና በከፍተኛ ሞራላዊ ልዕልና እንዳለ ሆኖ እነዚህን እሴቶች እንዲጠላቸው የሚሆነው በምን አይነት ርዕዮተ ዓለም ቢቀረፅ ነው? ቢንላደን ሙስሊም በመሆኑ ይሄ የምዕራቡ ዓለም እሴቶች ጥላቻ በእስልምና ሃይማኖት ዘንድ ብቻ ያለ ከመሰለን እጅግ ተሳስተናል።

በባለፈው ከፍል የቤት ስራ ሉድርጌ የወሰድኩት የተቃናውን የፈላሰፋው እጉዋለ “በተዋህዶ ከበረ” ፕሮጀክትን ለማቅረብ ነበር፡፡ ይሄን ለማድረግ የሚያስችለኝን መንገድ ለመጥረግ ደግሞ ምእራባዊውን ስልጣን ከሃይማኖትና ከፖለቲካ አንጻር መዳሰስ አስፈላጊ ሆኖ አገኝቼዋለሁ፡፡

ከሃይማኖት እና ከፖለቲካ አንፃር ስንመለከታት ይቺ የምንኖርባት ዓለም በሁለት ጐራ ከተከፈለች ከፍለዘመናት አልፈዋል- የምዕራቡ ዓለም (Occidental) እና የምስራቁ ዓለም (Oriental)። በተለምዶ የምዕራቡ ዓለም የሚባለው በዋናነት አሜሪካን እና አውሮፓን የሚወክል ሲሆን ሌሎች በነሱ የሥልጣኔ መንገድ እና የኑሮ ዘይቤ የሚመሩትን እንደ አውስትራልያ አይነቶችንም ይጨምራል። በአጠቃላይ በዚህ አውድ “ምዕራብ” ና “ምስራቅ” ማለት ጅኦግራፊያዊ አቀማመጥን ሳይሆን ርዕዮተዓለማዊ ወይም ፍልስፍናዊ ልዩነትን ነው የሚገልፀው።

በእርግጥ የምስራቁ ሃይማኖታዊ እሴቶች በምዕራብ ውስጥ እንዳሉ ሁሉ፤ የምዕራቡ ፖለቲካዊ እሴቶችም በምሥራቁ ዓለም አሉ። የሁለቱ ጐራዎች መሰረታዊ ፍሬ-ሃሳብ(Essence) ስንመለከት ግን፣ ምዕራብ ማለት የኑሮ ዘይቤውን በአመክንዮአዊ አዕምሮ(Reason) እና ከዚህ በሚመነጩት ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ፤ እንዲሁም በግለሰብ መብት ላይ ያተኮረ መንግሥት ምስረታ ላይ እና መንግሥት በግለሰብ ሂዎት ላይ የሚኖረውን ተፅዕኖ በእጅጉ የቀጨጨ ሲሆን፤ ምስራቅ ማለት ደግሞ የኑሮ ዘይቤውን ሃይማኖት ላይ እና ማህበራዊ ባህሎች እና እሴቶች ላይ የተመሰረተ፤ እንዲሁም በቡድን ወይም ጋርዮሽ (collective) መብት ላይ ያተኮረ መንግሥት ምስረታ ላይ እና መንግሥት በግለሰብ ሂዎት ላይ የሚኖረውን ተፅዕኖ እጅጉን የሰፋውን ይገልፃል።

የጥናት ትኩረታቸውን በዚህ ዙሪያ ያደረጉ ብዙ ተመራማሪዎች ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጀምሮ ምዕራባዊነት በአሜሪካ ጥላ ከለላ ስር ያለ ጉዳይ አድርገው ነው የሚወስዱት። ስለዚህ በአሁኑ ሰዓት የምዕራቡ ዓለም ጥላቻ በዋናነት የሚያነጣጥረው አሜሪካ ላይ ነው። በአጥኚዎቹ እይታ አሜሪካ እንድትጠላ ከሚያደርጓት አንዱ ምክንያት ከምታራምደው ፖሊሲ አንፃር ነው ይላሉ። ለምሳሌ ለፀረ ኮምዩኒስታዊ-አንባገነኖች ድርጅቶችን ድጋፍ መስጠትዋ፤እስራኤልን መደገፉዋ፤በትላልቅ ድንበር ተሻጋሪ ኮርፖሬሽኖችዋ አማካኝነት የምታደርገው የኢኮኖሚያዊ ሃብት ወረራ፤ IMFን እንደ የግል መሣሪያ መጠቀምዋ፤ በአጠቃላይ በሉላዊነት (Globalization) ሰበብ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም እንዲስፋፋ ማድረጉዋን ይጠቅሳሉ።

ሆኖም ግን፣ ይሄ አመለካከት ምዕራባዊው ዓለም በሞራል ልዕልና የሚጠላበትን ስረ-ነገር በትክክል አያሳይም። ምክንያቱም የአሜሪካም ሆነ የሌሎች ምዕራባውያን ሃገሮች መንግሥታት በሌሎች አገሮች ላይ ጣልቃ ለመግባት የሚያስችላቸውን ፖሊሲ፣ "ከምዕራባዊ እሴቶቻቸው የሚመነጭ ነው" ብለን ካልደመደምን በስተቀር ፤ ፖሊሲው መንግሥታቱ እንዲጠሉ ያደርጋቸው እንደሆን እንጂ፣ እንደው ባጠቃላይ ምዕራባዊውን የኑሮ ዘይቤ እንዲጠላ ሊያደርግ አይችልም።

ይልቅ በምስራቃውያን ዘንድ ምዕራቡ የሚጠላበት ዋናው ምክንያት "መንፈሳዊነትን በማዳከም ዓለማዊነትን ያለማምዳል" ከሚል እሳቤ ነው። ምንም እንኩዋ የምዕራብ ሳይንስን እና ቴክኖሎጂን በኑሮአቸው የሚመኙት ነገር ቢሆንም፤ ከዚህ ጋር አብሮ የምዕራቡን የኑሮ ዘይቤ ወደ ምስራቅ እንዳይሻገር በሀይለኛው የሚሰጉበት ጉዳይ ነው። ስጋታቸው የሃይማኖቶቻቸው (እዚህ ላይ እስልምና፣ ክርስትና፣ እና ኮሞዩኒዝምን ያጠቃልላል) ዶግማዎች እና ቀኖናዎችን አፈራርሶ ልቅ የሆነና እንዳሻው ባሰኘው መንገድ የሚጎርፍ ማህበረሰብ እንዲፈጠር ያደርጋል የሚል ነው። ከዚህ የተነሳ ደግሞ ሁሉም ሰው በሃይማኖት(ፓርቲ) ተቁዋማት(ድርጅት) ውስጥ ተሰባስቦ፣ በህብረት(Collectively) የሚያመልክበትን(ኢንዶክትርኔት የሚደረግበትን) ለዘመናት የቆየውን ባህላዊና ትውፊታዊ ሥርዓት አፈራርሶ፤ ሰው በግለሰባዊነት (Individualism) መንፈስ የራሱ የሆነ የግል መንፈሳዊነት እንዲለማመድ በር ይከፍትለታል የሚል ስጋት ነው። ለምሳሌ የኢትዮጵያ ኦሮቶዶክስ ቤተ ክር የፕሮቴስታንት እምነትን የምትከስበት አንዱ ጉዳይ የምዕራብ መጤ ሃይማኖት ስለሆነ የግል መንፈሳዊነትን ማለማመድ እና ማስፋፋት ነው አላማው የሚል ይገኝበታል። (ማቅ የተሃድሶ መናፍቃን ዘመቻ ገጽ 29)

በክፍል ፪ ጽሑፌ ለማሳየት እንደሞከርኩት፣ በፍልስፍና ደረጃ ይሄ ሰውን ማዕከል ያደረገው፣ በሥነ-ፍጥረት ጀምሮ በሥነ-ፍጥረት የሚጨርሰውን፣ ደስታውን እዚህ ምድር ላይ ለመጎናጸፍ የሚጥርን፣ መንፈሳዊነትን በራሱ አምክንዮአዊ ህሊና ውስጥ ምድር ላይ የተከለውን ምዕራባዊ ሥልጣኔ እና አምላክን ማዕከል ካደረገው፣ ደስታውን በወዲያኛው ዓለም ለመጎናጸፍ ተስፋ ከሚያደርገው፣ መንፈሳዊነትን ከልዕለ-ተፈጥሮ (Super-natural) አካል በተአምራታዊነት እና በብሕትውና ላይ ከተከለው ምሥራቃዊ (ወይም በአትናቲዮሳዊ ክርስትና ጫና ስር ያለውን ኢትዮጵያዊ) ሥልጣኔ ጋር ማዋሃድ እንደማይቻል ነው።

ይህንን የተገነዘበው (በጋዜጠኛ ነፍሱ) እጉዋለ፣ በፈላስፋ ሳይሆን በፖለቲከኛ መፍትሔ (በቅርቡ ብሩህ አለምነህ ያመጣው አገላለፅ) ነው የበተዋህዶ ከበረ ፕሮጀክቱን የቁዋጨው። የፖለቲካ መፍትሔ የሚለው ሃሳብ ለኔ በጣም ገላጭ ሃሳብ ነው። ምክንያቱም እጉዋለ "ፍሩህከ ንበር" በሚል መርህ ውስጥ የምዕራቡ ሥልጣኔን በኢትዮጵያ ሥልጣኔ መሠረትነት ላይ ተቀፅላ ሆኖ፣ ፈርቶ እና ተገዝቶ እንዲኖር የሚያደርግ ሥርዓትን ነው የጠቆመው።

ለመሆኑ "የምዕራቡ ሥልጣኔ መፍራት ያለበት ለምንድነው?" ወይም ደግሞ "የምዕራቡ ሥልጣኔ በምን መስፈርት ነው የፍርሃት እና የመገዛት ብይን የሚሰጠው?" የሚል ጥያቄ ቢነሳ፣ መልስ ብሎ የሚነግረን ከመጽሐፍ ቅዱስ የጳውሎስን ጥቅስ ነው። እዚህ ላይ ሳይመልሰው ሾላ በድፍን ብሎ ያለፈው አንድ ጥያቄ አለ:: "ምዕራባዊው ሥልጣኔ እኮ በመጽሐፍ ቅዱስ አይገዛም? እንዴት ነው የምዕራባዊ ሥልጣኔ የኑሮ ዘይቤ የሚከተልን ሰው፣ ለመጽሀፍ ቅዱስ ተገዝቶ ፈርቶ የሚኖረው?" የሚል ጥያቄ ቢነሳ ወደድንም ጠላንም መልሱ የሚሆነው "ራሱን ለመጽሐፍ ቅዱስ የሚያስገዛ መንግሥት ያስገደድዋል" የሚል ይሆናል። ፖለቲካዊ መፍትሔ ይልሃል ይሄ ነው!

እጉዋለ በጋዜጠኝነቱ በኦርቶዶክስ ቤተ ክር ጫና ስር ያለውን ሥልጣኔ ደግፎ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር አያያዘው እንጂ፣ ይህንን መፍትሔ ሃሳብ ለኢትዮጵያ ከማቅረቡ ቀደም ብሎ ሰለ አገራቸው ትውፊታዊ ባህል ቀናኢ ነን ያሉ ከተለያየ የሙያ መስክ የተውጣጡ ጃፓናውያን ምሁራን እአአ በ1942 ኪዮቶ ላይ ተሰባስበው ተመሳሳይ ፖለቲካዊ መፍትሔ አስቀምጠው ነበረ።

ምናልባትም እንደ ከበደ ሚካኤል ያሉ ሰዎች በ50ዎቹ ወቅት የስልጣኔ ዘይቤአችንን የጃፓን መንገድ እንዲከተል ደጋግመው ሲሰብኩ የነበሩት ከዚህ የተነሳ ነው::

ጃፓኖቹ ምሁራን የተስማሙበት ፍሬሀሳብ እንዲህ የሚል ነበር:-

ትውፊታዊው ጃፓናዊ ባህል ጥልቅ መንፈሳዊነት ያለው ሲሆን ዘመናዊው ምእራባዊ ስልጣኔ ግን ጥልቀት የሌለው ግልብ፣ መሰረተ-አልባ (rootless)፣የፈጠራ ሀይል የሚገድል ነው:: በተለይም ደግሞ አሜሪካ መሰረተ-አልባነትዋ፣ ቅይጥነትዋ፣ ማተሪያሊስትነትዋ፣ፋሽን አፍቃሪነትዋ ወዘተ ተደማምረው ነፍስ የሌለው ስሜት-አልባ ማህበረሰብ የተሸከመች ነች::

ይሄም ሆኖ፤ ምንም እንኩዋ ምንጩ ምእራባዊ ቢሆንም ዘመናዊነት በራሱ ግን ክፉ አይደለም፤ በጎነት ያለው ነው። በጎነቱም ለምእራባውያን ብቻ አይደለም፤ በጎነቱ ለመላው የሰው ዘር የሚሆን ነው። ስለ ዓለማችን ያለንን እውቀት እጅግ እንዲሰፋ አድርጎአል። ሀብት፣ ምቾት፣ ደህንነት፣ እና ጤና በእጅጉ እንዲጨምሩ አድርጎአል። ሰዎች በብልፅግና መንገድ እንዲራመዱ የሚያስችሉ ተቁዋማትን ፈጥሮአል። ችግር የሆነብን ወጣቱ ትውልድ ምእራባዊውን ስልጣኔ

ሳያላምጥ እየዋጠው ስለሆነ፣ ሳያላምጡ የዋጡት ምግብ ያለመፈጨት ችግር እንደሚያጋጥመው ሁሉ ወጣቱ ትውልድም የእውቀት አለመፈጨት ችግር እያጋጠመው ነው። "ስለዚህ" አሉ ተሰብሳቢዎቹ ምሁራን፣ "መፍትሄ መሆን ያለበት ወጣቱ ትውልድ የምእራቡን ኢመንፈሳዊነት አስወግዶ ዘመናዊነቱን ግን ሳይጥል ቀድሞ ወደ ነበርንበት ልእልና ያለው መንፈሳዊነት የሚመልስ መሆን አለበት።"

ይሄ ሃሰብ መግቢያዬ ላይ ከጠቀስኩት የአሳማ ቢንላደን ሃሳብ ጋር ጥልቅ የሆነ ዝምድና አለው። በጣም የሚገርመው ደግሞ ምሁራኖቹ ይሄን ምክረ ሃሳብ ያመጡት ጃፓን የአሜሪካ ፒርል ሀርቦር የጦር ካምፕን ከደበደቡት በሁዋላ መሆኑ ነው። ልክ ቢንላደን አሜሪካ ላይ የሽብር ጥቃት ካደረሰ በሁዋላ እንዳደረገው ንግግር- ከአሜሪካ ጥቃት በሁዋላ የተሰነዘሩ ሃሳቦች።

እዚህ ላይ ቢንላደንም ሆነ የጃፓኖቹ ምሁራን፣ የአሜሪካ ፖሊሲ አይደለም የሚያሳስባቸው። በግለሰባዊነት (Individualism) ላይ የተመሰረተውን ምእራባዊው ሞራሊቲን ነው እንጂ። ሁለቱም አሜሪካ ላይ የሚያነጣጥሩበት ወናው ጉዳይም፣ ምእራባዊው መንፈስ በአሜሪካ ውስጥ ጎልቶ ስለሚታይ ነው። ማለትም በቢንላደን ቁዋንቁዋ፣ "ምእራባዊ ስልጣኔ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ከታዩት ስልጣኔዎች እጅግ የከፋው ነው።" ምክንያቱም "ነፃነት"፣ "ሰብአዊ መብት"፣ እና ሰብአዊነት በሚል ጥላ ስር፣ ለጃፓኖቹ ምሁራን ግለሰባዊነትን፤ ለቢንላደን ደግሞ ምድራዊነትን ስለሚያስፋፋ።

እውነት ነው ጃፓኖች ዘመናዊነት የሚያጎናፅፈውን ምድራዊ ምቾት ስለማይጠሉት፣ እንደ ቢንላደን የዘመናዊነት ተምሳሌት የሆኑትን ሰማይ ጠቀስ ፎቆችን ማፈራረስ ላያስፈልጋቸው ይችል ይሆናል። ምናልባትም ደግሞ ከላይ እንደተጠቀሰው ልባቸው ወደ ምእራቡ ግለሰባዊነት የሸፈተባቸው ዜጎቻቸውን የሚቀጣ መንግስት በማቁዋቁዋም የዘመናዊነትን ፀጋዎች ሳይጉዋደልባቸው የሚኖሩበትን ማህበረሰባዊ ስርዓት በመዘርጋት የምእራቡ ዘመናዊነት ስጋት አይሆንብንም ብለው ስላሰቡ ሊሆን የችላል።

"እውነተኛው እና ቁዋሚ የሆነው አገራችን በሰማይ ነው፤ ምድር ጊዚያዊ መጠለያችን ነች" ብሎ የሚያምነው ሀይማኖተኛው ቢንላደን ግን፣ ምእራባዊ ዘመናዊነትን ከጃፓኖቹ ምሁራን በላይ የተረዳው ይመስላል። ይህውም የትኛውንም የመንግስት ዓይነት ቢመሰርቱ፣ ምእራባዊውን ዘመናዊነት፣ በከፊልም ቢሆን፣ ማስገባት (Import ማድረግ) ከተፈቀደ፣ መንግስት በግለሰቦች ሂወት የሚያደርሰውን የሳንሱር ጫና በጊዜ ሂደት እንደሚሸረሸር እና በመጨረሻም ግለሰቦች በትውፊታዊው ዶግማ መገዛት አቁመው ትወፊቱ ሊጠፋ ሁሉ እንደሚችል ቢንላደን ከማንም "ሀይማኖተኛ ነኝ" ባይ በላይ በደንብ የተገነዘበው ይመስላል። ምክንያቱም ሞሮኮአዊው ፈላስፋ አብዱ ፍላሊ አንሳሪ (Abdu Filali-Ansary) እንዳለው፣

"ዘመናዊነት ማለት ሰዎች ከዓለም ጋር እና ከራሳቸው ጋራ የነበራቸውን ዝምድና በአዲስ መልክ የቀየሩበት ማለት ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ በሳይንስ አማካኝነት ብዙ ነገሮች፣ እንደ የአየር ሁኔታ እና በሽታዎች ጭምር የእድል እጣፈንታ ጉዳይ እንዳልሆኑ የተገነዘቡበት ነው። ማህበረሰባዊ ስርዓትንም ለመለወጥ አስቸጋሪ ወይም የማይቻል እንዳልሆነ የሚገነዘቡበት ነው። በአብዮት አማካኝነት ጨቋኞችን ማስወገድ ይቻላል። ... ዴሞክራሲ እና ሰብአዊ መብቶቹ የሰው ልጅ የተጎናፀፋቸው የቅርብ ጊዜ ድሎች ናቸው። በእርግጥ ምእራባዊ ተብለው የሚታወቁ እሴቶች ሁሉን አቀፍ (Universal)" ናቸውና።

"ስልጣኔ ማለት" ትላለች አይን ራንድ ደግሞ "ማህበረሰብ ከተቡዋድኖ ኑሮ ወደ ግላዊ ኑሮ የሚያደርገው ጉዞ ነው። ከጫካ ኑሮ ያልወጣ ሰው (savage) ኑሮው በጎሳ ህግ የሚመራ የአደባባይ ኑሮ ነው። ስልጣኔ ማለት ሰውን ከሰዎች ነፃ የሚያወጣ ሂደት ነው።"

እንግዲህ ሀይማኖተኛው ቢንላደን ይህንን የዘመናዊነት እንደምታ ሲረዳ ነው "የነፃነት፣ ሰብአዊ መብት፣ እና ሰብአዊነት" ተምሳሌት የሆኑትን ነገሮች ኢላማ እንዲሆኑ ያደረገው። ልብ ብለን ስናስተውል ይለናል አሜሪካዊው ፈላስፋ ዴቪድ ኬሊ(David Kelley)፣"የአልቃይዳ ጠላፊዎች ኢላማ ያደረጉት የምእራባዊ ክርስትና ዋና መናህሪያ የሆነችውን እና መሪዎችዋ በአንድ ወቅት መሰሎቹ ላይ የመስቀል ጦርነት አውጀውባቸው የነበሩት ቫቲካንን አይደለም። ወይም ደግሞ ከ የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት በሁዋላ በመካከለኛው ምስራቅ ላይ የቅኝ ግዛት ፖሊሲ ስታራምድ የነበረችውን የእንግሊዘን የውጭ ጉዳይ መስሪያቤት ህንፃን አይደለም ኢላማ ያደረጉት። ይልቅ የኢንጅኔሪንግ እና የአለም ንግድ አድማስ የኩራት ምልክት የሆነውን፣ ከተለያዩ አገራት (በእስልምና የሚመሩ አገራት ሳይቀር) መጥተው በሰላምና በነፃነት ሀብት የሚፈጥሩበት እና የነዋይ ኢንቨስትመንት የሚያከናውኑበትን የዓለም

ንግድ ማዕከልን ነው ኢላማ ያደረጉት። በተመሳሳይ መልኩ የሃማስ አጥፍቶ ጠፊ ቦምብ አፈንጂዎች የእስራኤል ቤተ መቅደስን ሳይሆን ኢላማ የሚያደርጉት የፒዛ ቦታዎችን፣ ሆቴሎችን፣ የምሽት ክበቦችን ነው። ባጭሩ ኢላማቸው የሚያተኩረው የዘመናዊነት ቤተ መቅደሶችን ነው።”

ጠለቅ ብለን ስንመለከተው “ኑሮአችን በሰማይ ነው” ለሚሉት ሀይማኖተኞች ስጋታቸው ሌላ ተቀናቀኝ ሀይማኖት እንዳልሆነ እንረዳለን- ሀይማኖትን የሚቀናቀነው ምእራባዊው ዘመናዊነትን እንጂ። “ኑሮአችን በልጅ ልጆቻችን ነው” ለሚሉት የጋርዮሽ (Collectivism) ማህበረሰባዊ ስርዓት አራማጆች ደግሞ ስጋታቸው ሌላ ተቀናቃኝ የመንግስት ፖሊሲ ሳይሆን የጋርዮሽ ስርዓትን የሚቀናቀነው በግለሰባዊነት (Individualism) የተመሰረተው ምእራባዊ ዘመናዊነትን እንጂ።

ለመሆኑ ግለሰብ (Individual) እና ግለሰባዊነትን (Individualism) በሃይማኖት (Religion) እና በጋርዮሽ ማህበረሰብ (Collectivism) ዘንድ እጅግ የተጠላ እንዲሆን ያደረገው ነገር ምንድን ነው? ለምን?

መልሱ ረዘም ስለሚል በሚቀጥለው ክፍል እንመለከተዋለን።።

ሰላም

በምስራቅ አፍሪካ ዳርቻ ሰማይ ላይ(ክፍል 4)

በክፍል ፫ ላይ በምስራቃውያን ዘንድ ምዕራቡ የሚጠላበት ዋናው ምክንያት፣ ከሃይማኖት አንፃር ስንመለከተው "መንፈሳዊነትን በማዳከም ዓለማዊነትን ወይም ምድራዊነትን ያለማምዳል" የሚል ሲሆን ከጋርዮሽ(collective) ሥርዓት አራማጆች አንፃር ስንመለከተው ደግሞ "ግለሰባዊነት፣ ምዕራባውያንን ሞቅታ ካለው እና ተፈጥሮአዊው ማህበራዊ-ትስስር (communal relationship) አስወጥቶ ትርጉም ወደሌላቸው የተነጣጠሉ አተሞች(atoms) አሳንሶአቸዋል" የሚሉትን ጭብጦች ተመልክተናል።

በዚህ ክፍል የምንመለከተው ደግሞ "ምስራቃውያን የምዕራቡን የአኗኗር ዘይቤ በሞራላዊ ልዕልና እንዲያቃልሉት እና እንዲከሱት ያስቻላቸው ሞራላዊ መሠረት ምንድን ነው?" የሚል ይሆናል። በዚሁ መንገድ አልፈን ዋናው ግባችን ወደሆነው የእጉዋለን በተዋህዶ ከበረ ፕሮጀክት ሃሳቡን የምናቃናበት አውድ እንደርሳለን።

አንድን ሰው መንገድ ላይ አስቁማችሁ "ሞራሊቲ ማለት ምን ማለት ነው?" ብላችሁ ብተጠይቁት፣ "ሞራሊቲ ማለት እማ ራስን ለሌሎች አሳልፎ ወይም መስዋዕት አድርጎ ማቅረብ ማለት ነው" ብሎ እንደሚመልስ አያጠራጥርም። ይሄ የሞራሊቲ ፍቺ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በምድር ላይ ያሉ አብዛኞቹ ሰዎች ይቀበሉታል ተብሎ የሚወሰድ ሃቅ ነው።

ሰዎች የሌላ-ቅድሚያነት(Altruism) አስተምህሮዎችን "እውነት ናቸው" በሚል ብቻ ሳይሆን የሚቀበሉዋቸው እውነትነታቸው ምንም አይነት ማስረጃ የማይጠየቅባቸው በራሳቸው በቂ ማስረጃ የሆኑ (self-evident) ናቸው በሚል እሳቤ ነው።

ለሌሎች ጥቅም ሲባል የሚሰራን ሥራ በጎ-ምግባረ-እሴት (virtuous) ሲሆን ለራስ ጥቅም ተብሎ የሚሰራ ሥራ ግን ምናልባት የሚያስኮንን ባይሆንም የሚያስወድስ ምግባረ-እሴት(virtue) ተደርጎ ግን በፍጹም አይወሰድም።

ልክ በዚህ ዘመን "መሬት እኮ ጠፍጣፋ ልትሆን ትችላለች" ብሎ የሚከራከርን ሰው "ከሳይንስ እዉቀት ፅዱ" ተብሎ እንደሚሳቅበት ሁሉ፤ "የሌላ-ቅድሚያነት(altruism) አስተምህሮ እኮ ስህተት ነው" ብሎ የሚከራከር ሰውም ማህበረሰባዊ ዕውቀት የጐደለው ጨቅላ ተብሎ ሊሳቅበት ወይ ሊታዘንለት፣ ወይም ደግሞ የሌሎች ላብ መዝብሮ ሃብት ለማግበስበስ የሚፈልግ ስግብግብ ወይም ራስ ወዳድ(selfish) ተብሎ ሊገለል ይችላል።

ለሌላ-ቅድሚያነት (altruism)፣ እርስ በራሳችን ከመበላላት አድኖ ጤነኛ ማህበረሰብ ለመመስረት የሚያስችል የግብረ ገብ ትምህርት ተደርጎ ነው በስፋት የሚሰብከው።

መፈቀሬ-ፍልስፍና ግን ይጠይቃል "እውነት ለሌላ-ቅድሚያነት (altruism) ጤነኛ ማህበረሰብ እንዲመሰረት ያስችላልን? ሌላ ጤነኛ ማህበረሰብ እንዲመሰረት የሚያስችል የግብረገብ ትምህርትስ የለምን? ለምሳሌ ከ ለሌላ-ቅድሚያነት (altruism) ራስወዳድነት (selfishness) የተሻለ የማይሆንበት ምክንያት ምንድን ነው ?"...

እዚህ ላይ "ተው! ተው! ራስወዳድነት ደግሞ እርስበርሳችን እንድንጠፋፋ ሊያደርግ ካልሆነ በስተቀር እንዴት ነው ጤነኛ ማህበረሰብ እንዲመሰረት የሚያደርገው?" የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም።

"እርግጠኞች ናችሁ? እስቲ የራስወዳድነትን ፍቺ መዝገበቃላት ላይ ተመልከቱ" ትለናለች አይን ራንድ በ The Virtue of Selfishness መጽሐፍዋ።

አይን ራንድ ያብራራችውን እንደሚከተለው ተርጉሜ አቅርቤዋለሁ።

<ትእምርተ ጥቅስ>

በአብዛሀኛው አጠቃቀም "ራስወዳድነት" የሚለው ቃል ከክፋት ጋር አቻ ትርጉም ነው የሚሰጠው። በአእምሮ ውስጥ የሚፈጥረው ምስልም የራሱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በሬሳ ክምር ላይ የሚረማመድ፣ ከአሁን አሁን ሊሚፈጠሩበት የአዕምሮቢስ ቅጽበታዊ ፍላጎቶቹን ለማርካት የሚታትር፣ እና ለማንኛውም ሕይወት ያለው አካል ግድ የሌለው አረመኔ ገዳይ ምስልን ነው።

ሆኖም "የራስወዳድነት" ትክክለኛ ትርጉም እና የመዝገበቃላት ፍቺው የራስ-ፍላጎቶችን(self-interest) ጉዳዬ ብሎ መያዝን ነው።

ይህ ጽንሰሃሳብ በውስጡ የሞራል ግምገማን አያካትትም። የራስ-ፍላጎትን ጉዳዬ ብሎ መያዝ በጎም ይሁን ክፉ የሚነግረን ነገር የለም። እርግጠኞቹ የሰው ፍላጐቶችም ከምን እንደሚፈጠሩ አይነግረንም። ለእንደዚህ ዓይነት ጥያቄዎች ምላሽ መስጠትን ደግሞ የግብረገብነት ትምህርት ተግባር ነው።

የለሌላ-ቅድሚያነት(altruism) ግብረገብ ትምህርት ግን እነዚህን ጥያቄዎች ሲመልስ በአዕምሮአችን ውስጥ የአውሬ ምስል እንዲፈጠር አድርጎአል። ይሄም ያደረገው ሰዎች ሁለት ኢሰብዓዊ አስተምህሮዎቸን እንዲቀበሉ ለማድረግ ነው:- ሀ) ፍላጎቶቹ ምንም ይሁኑ ምን የራስ-ፍላጎትን ጉዳዬ ብሎ መያዝ ክፉ እንደሆነ እና ለ) የአውሬ ተግባራት የሚባሉት በእርግጥም ለራስ-ፍላጎት ተብለው የሚከወኑ ተግባራት (እዚህ ላይ ለባልንጀራው ሲል መተው የነበረበትን የሚል ክስ ያስገባል altruism) መሆናቸውን።

ለሌላ-ቅድሚያነት(altruism) ለሌሎች ጥቅም ሲባል የሚሰራ ስራን በጎ ሥራ እንደሆነና ለራስ ጥቅም ሲባል የሚሰራ ስራን ደግሞ መጥፎ እንደሆነ ያውጃል። ለዚህም የአንድን ድርጊት ተጠቃሚን (beneficiary of an action) ብቸኛው የሞራላዊ እሴት ክራይቴሪያ አድርጎ ይወስደዋል። እናም የአንድን ድርጊት ተጠቃሚ የድርጊቱ ባለቤት አይሁን ብቻ እንጂ ከድርጊቱ የሚጠቀመው ሌላ አካል ከሆነ ድርጊቱ ሞራላዊ ይሆናል ማለት ነው።

<ትእምርተ ጥቅስ ተዘጋ>

አሁን በክፍል ፫ ላይ በይደር ያቆየሁትን ጥያቄ እዚህ ላይ እናንሳው። ለመሆኑ ግለሰብ (Individual) እና ግለሰባዊነትን(Individualism) በሃይማኖት(Religion) እና በጋርዮሽ ማህበረሰብ(Collectivism) ዘንድ እጅግ የተጠላ እንዲሆን ያደረገው ነገር ምንድን ነው? ለምን?

በአጭሩ መልስ ለማስቀመጥ ከተፈለገ መልሱ የሚሆነው "ግለሰባዊነት(Individualism) በራስወዳድነት መርህ መሠረትነት ላይ የሚገነባ ማህበረሰባዊ ሥርዓት ስለሆነ እና ራስወዳድነትን ደግሞ አውሬ ተደርጎ እንዲቀረጽ ለሌላ-ቅድሚያነት(altruism) በብዙ ስለሰራ" የሚል ይሆናል።

ጉዳዩን በደንብ ለማብራራት ግን የግለሰባዊ-ሰው ነፍስ ምን እንደምትመስል መቃኘት ይኖርብናል። ይሄም የምናደርገው አሁንም ከአይን ራንድ The Fountainhead ልብወለድ መጽሐፍ ውስጥ ዋናው ገጸባህሪ ፍርድቤት ችሎት ላይ ቀርቦ ስለ ግለሰባዊ-ሰዉ ነፍስ በሰጠው ትንታኔ ነው። ከዚህ በሁዋላ ያለው በሙሉ የንግግሩ(speech) ትርጉም ነው። እነሆ በረከት!

የግለሰባዊ-ሰው ነፍስ

<ትእምርተ ጥቅስ>

ከብዙ ሺህ ዘመናት በፊት እሳት ማቀጣጠልን ያስገኘ የመጀመሪያው ሰው አለ። ምናልባት ወንድሞቹ የሚሆኑት ሌሎች ሰዎችን እሳት መለኮስ እንዴት እንደሚቻል ባስተማረበት የእንጨት ርብራብ ላይ ተቃጥሎ ሊሆን ይችላል። የሰው ዘር ከሚፈራው መንፈስ(ወይም ጋኔን) ጋር ግንኙነት ያለው ክፉ አድራጊ ተደርጎ ነው የተፈረጀው። ከዚያ በሁዋላ ግን እሳቱ ሰዎች ራሳቸውን የሚያሞቁበት፣ ምግባቸውን የሚያበስሉበት፣ ዋሻቸውን የሚያበሩበት ሆነላቸው። ይሄ የመጀመሪያው ሰው፣ እነሱ በአዕምሮአቸው ሊያስቡት ያልቻሉትን ገጸበረከት ትቶላቸው ሲያልፍም ጨለማን ከምድረገፅ እንዲገፈፍ አድርጎአል። ከዘመናት በሁዋላም የመጀመሪያው ሰዉ ተሽከርካሪን(wheel) ፈጠረ። ምናልባት ወንድሞቹ የሚሆኑት ሌሎች ሰዎችን እንዴት ተሽከርካሪ መስራት እንደሚቻል በሚያስተምርበት ንጣፍ ላይ ተሸረካክቶ ሞቶ ሊሆን ይችላል። ሰዎች ሊሻገሩት የማይገባ ድንበር የተሻገረ ወንጀል ተላላፊ ተደርጎ ነበር የተፈረጀው።ከዚያ በሁዋላ ግን ሰዎች ከአድማስ አድማስ መንገድ እያቆራረጡ መጓዝ ቻሉ። ይሄ የመጀመሪያው ሰው እነሱ በአዕምሮአቸው ሊያስቡት ያልቻሉትን ገጸበረከት ትቶላቸው ሲያልፍ የዓለም መንገዶች እንዲከፈቱ አድርጎአል።

ሁሉም የሰው ዘር ስለ ታሪካዊ አመጣጡ በሚተርክበት የአፈታሪክ መዝገብ ውስጥ ያ ሰው፣ ያ የማይንበረከከው እና የመጀመሪያው ሰው፣ የታሪክ መዝገቡ መክፈቻ ምዕራፎች ላይ እናገኘዋለን። እሳትን ያስገኘው ፕሮሜቲየስ ከአለት ጋር ታስሮ ስጋው በጥንብ አንሳዎች እንዲቦጫጨቅ ተፈርዶበታል፤ ምክንያቱም የአማልክት ንብረት የሆነውን እሳት

ሰርቆ ለሰው አስረክቦአልና። አዳም እንዲሰቃይ ተረገመ፤ ምክንያቱም ክፉ እና ደጉን ከምታሳውቀው የእውቀት ዛፍ በልቶአልና። የአፈታሪኩ ምንነት የፈለገው ቢሆን የሰው ዘርን የታሪክ ትውስታ ጥላ ተከትለን የሔልዮሽ ብንጓዝ የሆነ ቦታ ላይ የምናገኘው አንድ ታሪክ አለ። የሰው ዘር ከብሩ የሚጀምረው በአንድ ሰው እና ያ አንድ ሰው ስለ ድፍረቱ ወይም የመንፈስ ብርታቱ(courage) በከፈለው ዋጋ ነው።

በየዘመናቱ ከራሳቸው ርዕይ(vision) ውጪ ምንም ያልታጠቁ፤ በአዳዲስ መንገዶች ላይ የመጀመሪያ እርምጃ የተራመዱ ግለሰቦች ነበሩ። ዓላማቸው ቢለያይም በጋራ አንድ የሚያደርጋቸው ነገር ግን አለ። እርምጃው የመጀመሪያ፣ መንገዱ አዲስ፣ ርዕዩን ደግሞ ከማንም ያልተበደሩት፣ እናም በምትኩ ያገኙት ምላሽ ደግሞ ጥላቻ መሆኑ። ታላላቅ ባለ-ፈጠራዎች (creators)፤ አሰላሳዮች(thinkers)፣ አርቲስቶች፣ ሳይንቲስቶች፣ አስገኚዎች(inventors) በዘመናቸው ከነበሩት ሌሎች ሰዎች ጋር በብቸኝነት ተጋፍጠዋል።

ሁሉም አይነት ታላቅ አዲስ ሃሳብ ተቃውሞ ገጥሞታል። ሁሉም አይነት አዲስ ፈጠራ ተወግዞአል። የመጀመሪያው ሞተር የሞኝ ሥራ ተብሎአል። አውሮፕላን ማብረር ፈጽሞ የማይቻል ተደርጎ ተወስዶአል። ሃይል ማመንጫ እንደ ሰይጣናዊ ሥራ ተቆጥሮአል። ማደንዘዣ መድሃኒት እንደ ሀጢአት ተቆጥሮአል። ሆኖም ግን እነዚህ ርዕይን ከማንም የማይበደሩ ግለሰቦች ርዕያቸውን ይዘው ወደፊት ተራመዱ። ታገሉ፣ ተሠቃዩ፣ ከፈሉ፤ ግን ደግሞ አሸነፉ።

የወንድሞቹን ፍላጎት ለማርካት የሚነሳሳ አንድም ባለ-ፈጠራ የለም፤ ምክንያቱም ወንድሞቹ ሰዎች፣ ለዘመናት ከተላመዱት እና የህሊና ጥረት ከማይጠይቀው የየቀኑ የስራ ድግግሞሻቸውን ሊያላቅቃቸው ስለሆነ፣ ፈጠራውን የሚቀበሉ አይደሉማ። ለፈጠራ የሚያነሳሳው መነሾ ምክንያት የራሱ እውነት ነው። በራሱ መንገድ ሊያሳካው ለመረጠው ሥራ የተነሳሽነት መነሾ ምክንያቱ የራሱ እውነት ነው። ሲምፎኒም፣ መጽሐፍም፣ ሞተርም፣ ፊሎዞፊም፣ አውሮፕላን ወይም ህንፃም- ግቡም ሂዎቱም ፈጠራው ነው እንጂ፤ ሲምፎኒውን የሚያዳምጡት የመጽሐፉ አንባቢዎች፣ የሞተሩ ኦፐሬተሮች፣ የፍልስፍናው ተከታዮች፣ አውሮፕላኑን የሚበሩበት ወይም ሕንፃውን የሚኖሩበት ሰዎች አይደሉም። ፈጠራው እንጂ የፈጠራው ተጠቃሚዎች አይደሉም፣ ማለትም ፈጠራው እንጂ ሌሎች ከፈጠራው ስለሚያገኙት ጥቅም አይደለም ገፊ ምክንያቱ። የራሱን እውነት ቅርፀ-አካል ይዞ እንዲወጣ ያደረገበትን ፈጠራው ነው ዋናው። ከተቃዋሚዎቹም ይሁን ከምንም በላይ የራሱን እውነት ከፍ አድርጎ ይይዛል።

የርዕዩ፣ የጥንካሬው፣ የመንፈስ ብርታቱ ምንጭ ደግሞ የራሱ መንፈስ ነው። የሰው መንፈስ ደግሞ ራስነቱ(his self) ነው። ንቃተህሊናው(consciousness) የሆነው አካል ነው ራስነት። ማሰብ፣ ስሜት፣ ዳኝነት፣ ክዋኔ(to act) ደግሞ የኢጎ(Ego) ተግባራት ናቸው።

የፈጠራ ባለቤቶቹ ራስ-አልባ(selfless) አልነበሩም። የኢጎአቸው ራስ-ቻይነት (self-sufficient)፣ ራስ-አነሳሽነት (self-motivated)፣ ራስ-አንቀሳቃሽነት(self-generated) ነው ዋናው የሃይላቸው ምስጢር። ጥንተ-ምክንያታቸው(first-cause)፣ የኢነርጂ ምንጫቸው፣ የህይወት ሃይላቸው (life force)፣ ዋና አንቀሳቃሻቸው(prime mover) ነው- ራስነት-አቸው(ኢጎአቸው)። ባለ-ፈጠራ ሰው የማንንም የምንንም አገልጋይ አይደለም። ለራሱ ነው የሚኖረው።

ለራሱ መኖር በመቻሉም ለሰው ልጅ ክብር ያጎናፀፉትን ነገሮች ማስገኘት ችሎአል። ከፍተኛ የስኬት ውጤታቸው ባህሪም ይህን ይመስላል።

ሰው ያለ አእምሮው በሕይወት መቆየት አይችልም። ከማህጸን ወጥቶ ምድርን ሲረግጥ፣ ከአዕምሮው ውጪ ሌላ ምንም መሣሪያ ሳይታጠቅ ነው። እንስሳት ምግባቸውን በጉልበታቸው ያገኛሉ። ሰው ግን የጭልፊት አይነት ጥፍር፣ የነብር ወይም የአንበሳ አይነት ጥርስ፣ የእባብ አይነት መርዛማ ምላስ፣ ቀንድም ሆነ ጡንቻ ወዘተ የለውም። የዕለት ቀለቡን ወይ ዘርቶ ወይ አድኖ ማግኘት አለበት። መዝራት እንዲችል ደግሞ የሃሳብ ሰንሰለቶች ያስፈልጉታል። ከዚህ ከትንሹ ፍላጎት አንስቶ እስከ ሕይወቱን የሚመራበት ሃይማኖታዊ ረቂቅ ሃሳቦች፣ ከተሽከርካሪ እስከ ሰማይ ጠቀስ ፎቅ፣ ሁሉ ነገራችንም ሆነ አሉን የምንላቸው ሀብቶቻችን ከአንድ የሰው መለያ ባህሪ የሚመነጭ ነው- የአምክንዮአዊ ህሊናው ተግባር ወይም ሥራ።

ህሊና ግን የግለሰብ መለያ ባህሪ ነው። የጋርዮሽ (collective) አእምሮ የሚባል ነገር የለም። የጋርዮሽ ሃሳብ የሚባል ነገር የለም። ሰዎች በቡድን ሆነው የሚደርሱበት የጋራ ስምምነት ከብዙ ግለሰቦች ሃሳብ ጭማቂው (average) ተወስዶ፣ ወይም ደግሞ አስታራቂ ሃሳብ ቀርቦ የሚገኝ ሁለተኛ ደረጃ (secondary) ውጤት ነው። ጥንተ ተግባሩ- የአመክንዮው ሂደት- በእያንዳንዱ ግለሰብ ህሊና ውስጥ መከናወን አለበት። አንድን ምግብ ብዙ

ሰዎች እንዲካፈሉት ማድረግ እንችላለን፤ ነገር ግን በጋርዮሽ ጨጉዋራ መፍጨት የሚባል ነገር አይኖርም። ማንም ሰው በሌላ ሰው ሳንባ አይተነፍስም። ማንም ሰውም በሌላ ሰው አእምሮ አያስብም። ሁሉም የመንፈስም የአካልም ተግባራት ግላዊ ናቸው። ለሌላ ማጋራትም ሆነ ማስተላለፍ አይቻልም።

ከሌሎች ሰዎች የሃሳባቸው ፈጠራ ውጤቶችን ግን እንወርሳለን። ተሽከርካሪን ወርሰናል። ጋሪ ሰራንበት። ከጋሪው ወደ አውቶሞቢል ተሸጋገርን። ከአውቶሞቢል ወደ አውሮፕላን። በዚህ ሁሉ ሂደት ውስጥ ከሌሎች ሰዎች ያገኘነው ነገር ቢኖር የሃሳባቸው የመጨረሻ ውጤት የሆኑትን ፍሬዎቻቸውን (ወይም ምርቶቻቸውን) ነው። አንቀሳቃሹ ሃይል፣ የሌሎችን የፈጠራ ውጤት እንደ ግብአት ወስዶ የሚቀጥለውን የፈጠራ ደረጃ ለማስገኘት የሚያስችለው የአእምሮ የፈጠራ ፋኩልቲ ነው። ይሄ የፈጠራ ፋኩልቲ የሚሰጥ ወይም ደግሞ የምንቀበለው፣ የሚጋሩት ወይም ደግሞ የሚበደሩት ሊሆን አይችልም። ባለቤትነቱ የግለሰቦች ነው። በዚህ ፋኩለቲ አማካኝነት የሚፈጠረው ፈጠራ ደግሞ የባለ-ፈጠራው ንብረት ነው። ሰዎች አንዳቸው ከአንዳቸው ሊማሩ ይችላሉ። መማር ማለት ግን የግብአት ልውውጥ ማለት ነው። ማንም ሰው የማሰብ አቅሙን ለሌላ ሊሰጥ አይችልም። ይሄ አቅም ነው ግን በህይወት የመቆያ ብቸኛው መሳሪያችን።

እዚህ ምድር ላይ ለሰው የተቸረው ምንም ነገር የለም። የሚያስፈልጉት ነገሮች በሙሉ መመረት አለባቸው። እዚህ ላይ ነው እንግዲህ ሰው መሰረታዊ አማራጮቹን የሚጋፈጠው፡- ከሁለቱ በአንዱ መንገድ ነው መኖር የሚቻለው-። የህሊናው ጥረት በሆነው የግሉ ስራ፤ ወይም ደግሞ ሌሎች በህሊና ጥረታቸው በሚያስገኙት ላይ ጥገኛ ሆኖ፣ ማለትም ባለ-ፈጠራው ያመነጫል ጥገኛው ደግሞ ይዋሳል። ባለ-ፈጠራው ተፈጥሮን ብቻውን ይጋፈጣታል ጥገኛው ደግሞ ተፈጥሮን በመካከለኛ ሰው (ወይም በአማላጅ) ይጋፈጣታል።

ባለ-ፈጠራ ሰው ጉዳዩ ተፈጥሮን መቆጣጠር ሲሆን፤ ጥገኛው ጉዳዩ የሚያደርገው ደግሞ ሰዎችን መቆጣጠር ነው።

ባለ-ፈጠራ ሰው ስለ ስራው ይኖራል። ሌሎች ሰዎች አያስፈልጉትም። ተቀዳሚ ግቡ በውስጡ ነው ያለው። ጥገኛው ግን በሌላ-እጅ(second-hand) ነው የሚኖረው። ሌሎች ያስፈልጉታል። ጥንተ መነሾው (his prime motive) ሌሎች ናቸው።

የባለ-ፈጠራ ሰው መሰረታዊ ፍላጎት ግለ-ነፃነት (Independence) ነው። አመክንዮአዊ ህሊና በማንኛውም አይነት የሃይል ጫና ውስጥ ሆኖ መስራት አይችልም። ለምንም ነገር በልጉዋም ሊገራ፣ ሊሰዋ፣ ወይም ሊንበረከክ አይችልም። ለተነሳሽነትም ለስራም ሙሉ የሆነ ግለ-ነፃነት ያስፈልገዋል። ለባለ-ፈጠራ ሰው፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚኖረው ግኑኝነት ተቀዳሚ ጉዳይ አይደለም።

ለበሌላ-እጅ-ኖዋሪ(second-hander) ግን መሰረታዊ ፍላጎቱ የሚሆነው ራሱን ለመቀለብ የሚያስችለውን ከሌሎች ያለውን ዝምድና ማስጠበቅን ነው። ከሌሎች ጋር የሚኖረውን ግኑኝነት ተቀዳሚ ስፍራ ላይ ነው የሚያስቀመጠው። ሰው የሚኖረው ሌሎችን ለማገልገል ነው ሲልም ያውጃል። ለሌላ-ቅድሚያነትን (Altruism) ይሰብካል።

ለሌላ-ቅድሚያነት (Altruism) ማለት ሰው ሌሎችን ከራስ በላይ በማስቀደም ስለ ሌሎች እንዲኖር የሚያስገድድ ዶክትሪን ነው።

ማንም ሰው ስለ ሌላ መኖር አይችልም። አካሉን ለሌላ ማጋራት እንደማይችል ሁሉ፣ መንፈሱም ለሌላ ማጋራት አይችልም። በሌላ-እጅ-ኖዋሪው (second-hander) ግን የሞራሊቲ መርሆችን ገልብጦ ለሌላ-ቅድሚያነትን ከሌሎች አለአግባብ የሚጠቀምበት መሳሪያ አድርጎ ይጠቀምበታል። ከዚህ የተነሳም ሰዎች የባለ-ፈጠራ ሰውን የሚያጠፉ እሳቤዎችን ለዘመናት ሲሰበኩ ነው የኖሩት። ለዘመናት ሰው በሌላ ላይ ጥገኛ መሆንን (dependence) እንደ በጎ ስራ (virtue) ነው ሲሰበኩ የኖሩት።

ስለ ሌሎች ብሎ ለመኖር የሚሞክር ሰው ሂዎቱ በሌሎች ምርኩዝነት ላይ የተመሰረተ ነው። ገፊ ምክንያቱ በሌሎች ጥገኝነት ላይ የተመሰረተ ስለሆነ የሚያገለግላቸው ሰዎችም በርሱ ላይ ጥገኛ እንዲሆኑ ያደርጋል። በዚህም በጋራ ከመማሰን (corruption) ውጪ ከግኑኝነቱ የሚገኝ ፍሬ አይኖርም። በፅንሰሀሳብ ደረጃም የማይቻል ነው። በገሃዱ ዓለም ከታየው ለዚህ አይነት መንገድ እጅግ የሚቀርበው- ሌሎችን በማገልገል የሚኖር ሰው ባርያን ነው። ታድያ የጉልበት ባርነት ዘግናኝ ከሆነ፣ የመንፈስ ባርነትስ ምንያክል ሊዘገንን ይችላል? እንዲያውም በምርኮ ላይ ያለን ባርያ የሰውነት ክብር ምልክት ይታይበታል። ይሄውም ያለበትን ሁኔታ ክፉ አድርጎ የመመልከት እና የመቃወም

ዕድል ያገኛልና። በፍቅር ስም፣ በፈቃዱ ራሱን ለሌሎች ባርያ አድርጎ የሚሰጥ ሰው ግን ወራዳ ፍጥረት ነው። የሰው ክብርን እና የፍቅርን ፅንሰሃሳብ ያዋረደ ሰው ነው። ይሄ ግን የለሌላ-ቅድሚያነት(Altruism) ዋና መሰረተ ሃሳብ ነው።

ሰዎች ለዘመናት የተሰበኩት የምግባረ-እሴት(virtue) ከፍተኛ ደረጃ አንድን ነገር ከግብ ማድረስን ሳይሆን መስጠትን ነው።ሆኖም አንድ ሰው ያልተመረተን (ወይም ያልተፈጠረን) ነገር ሊሰጥ አይችልም። ማምረት ከማከፋፈል ይቀድማል፤ አለበለዚያ የሚከፋፈል ነገር አይኖርም። ከማንኛውም ዓይነት የተጠቃሚ ፍላጎት በፊት የባለ-ፈጠራ ፍላጎት ይቀድማል። ሆኖም ስጦታዎችን እውን እንዲሆኑ ካደረገው ባለ-ፈጠራ በላይ ስጦታዎችን የሚያድለው በሌላ-እጅ-ኖዋሪውን እንድናደንቅ ነው ለዘመናት የተሰበክነው። ምፅዋትን እናሞግሳለን፤ የስራ ውጤትን (achievement) ላይ ግን ትኬሻቸንን በቸልተኝነት እነሰብቃለን።

ሰዎች ለዘመናት የተሰበኩት፣ ተቀዳሚ ጉዳያቸው የሌሎችን ስቃይ ማቃለልን እንዲሆን ነው። ስቃይ ግን በሽታ ነው። የሆነ ሰው ህመም ላይ ቢወድቅ ሌላ ሰው ማስታመም እና እርዳታ ለመስጠት ይሞክራል። ከዚህ በዘለለ ይሄንን አድራጎት ከፍተኛው የምግባረ-እሴት *መመዘኛ* አድርጎ *መውሰድ* ግን የህይወት ወሳኙ ክፍል ስቃይ አድርጎ መውሰድ ይሆናል። ለዚህም አንድ ሰው በጎ አድራጊ እንዲሆን ሌሎች ሲሰቃዩ ማየትን ሊመኝ ግድ ይለዋል ማለት ነው። እንግዲህ የሌሎች-ቅድሚያነት ትክክለኛ ባህርይ ይሄ ነው። ባለ-ፈጠራ ሰው ጉዳዩ ከበሽታ *ጋር* ሳይሆን ከህይወት *ጋር* ነው። አሁንም ግን የባለ-ፈጠራ ሰዎች ስራ ነው ለሌላ-ኖዋሪዎች ሊያስቡት ከሚችሉት በላይ የተለያዩ አካላዊም ሆነ የመንፈስ በሽታዎችን አንድ በአንድ እያጠፉ የሰውን ልጅ ስቃይ ይበልጥ እንዲቃለል ያደረገው።

ሰዎች ለዘመናት የተሰበኩት ሌሎች ሰዎች በሚሉት ሁሉ ተስማምቶ መኖርን ምግባረ-እሴት እንደሆነ ነው። ባለ-ፈጠራ ሰው ግን አልስማማም ማለትን የሚችል ነው። ሰዎች የተሰበኩት የማዕበሉን አካሄድ እያዩ መዋኘትን ጥሩ ነገር እንደሆነ ነው። ባለ-ፈጠራ ሰው ግን ከማዕበሉ በተቃራኒ የሚጉዋዝ ነው። ሰዎች የተሰበኩት በህብረት መቆም ምግባረ-እሴት እንደሆነ ነው። ባለ-ፈጠራ ሰው ግን ብቻውን መቆም የሚችል ነው።

ሰዎች ለዘመናት የተሰበኩት ኢጎ (Ego) ከክፋት *ጋር* አቻ እነደሆነ ነው። ራስ-አልባነት(Selflessness) ደግሞ የምግባረ-እሴት ድንቅ ተምሳሌት እንደሆነ። በትክክለኛ ትርጉሙ ሲወሰድ ባለ-ፈጠራ ሰው ኢጎአዊ (Egoist) ነው። እንዲሁም በትክክለኛው ትርጉሙ ራስ-አልባ ሰው የማያስብ፣ ስሜት-አልባ፣ የማይፈርድ፣ ወይም ድርጊት-አልባ ማለት ነው። እነዚህ የራስነት (Self or Ego) ተግባራት ናቸውና።

እዚህ ላይ የተገለበጠው መሰረታዊ ነገር አደገኛ ነው። መጀመሪያ የፅንሰሃሳቡ ፍሬ-ነገር(essence) ስንኩል እንዲሆን ተደረገና፣ ሰው አማራጭ የሌለው እንዲሆን ሆነ፣ ነፃነትም አጣ። የበጎ እና የክፉ ዋልታ የሆኑ ሁለት ፅንሰሀሳቦች ለምርጫ ቀረቡለት፡- ራስወዳድነት(selfishness) እና ለሌላ-ቅድሚያነት(altruism)። ራስወዳድነትን ሌሎችን ለራስ ጥቅም መስዋእት አድርጎ ማቅረብን ተደርጎ ተወሰደ። ለሌላ-ቅድሚያነት ደግሞ ራስን ለሌሎች ጥቅም መስዋእት አድርጎ ማቅረብን ሆነ። ይህ ዓይነት አማራጭ ሰዎችን ከስቃይ ውጪ ሌላ ምርጫ የሌላቸው አድርጎ በማይሻር ቁዋጠሮ፣ ሌሎች ሰዎች ላይ ጥገኛ አድርጎ፣ ጠፍርጎ አሰራቸው። አማራጭ ሆነው የቀረቡለት፣ ሰው ለሌሎች ጥቅም ሲባል የሚሸከመው ስቃይ ወይም ደግሞ ሌሎች ለሱ ሲሉ የሚቀበሉት ስቃይ ሆኑ። ሰው ደስታን ማግኘት ያለበት ራሱን በማዋረድ ነው የሚል ስብከት ሲታከልበት ደግሞ የአማራጭ በሩ እንዲዘጋ ሆነ። የቀረው ብቸኛ አማራጭ ሌሎችን በመቅጣት መኖር ነው የሚል ማስፈራሪያ ሲቀርብለትም ሰው ራሱን መቅጣትን እንደ ድንቅ ተምሳሌት ሊወስደው ግድ ሆነበት።

ይሄ፣ የሰው ዘርን ያታለለ ከፍተኛው ማጭበርበር ነው።

ይሄ፣ ጥገኝነት እና ስቃይ የህይወት መሰረታዊ በህሪያት ሆነው ለዘመናት ተጠብቀው እንዲቆዩ ያደረገ ዘዴ ነው።

ምርጫው ግን ራስን መስዋእት ማድረግ ወይም በሌሎች ላይ መንገስን አይደለም መሆን ያለበት። ምርጫው ግለ-ነፃነትን ወይም ደግሞ ጥገኝነትን ነው። የባለ-ፈጠራ ህግ ወይም ደግሞ የበሌላ-እጅ-ኖዋሪ ህግ። መሰረታዊው ጉዳይ ይህ ነው። በህይወት ወይም በሞት አማራጮች ላይ የሚመሰረት ጉዳይ ነው። የባለ-ፈጠራ ህግ የሚገነባው ሰው በህይወት እንዲቆይ ከሚያስችል ምክንያታዊ አእምሮ ውስጥ ካሉት ፍላጎቶች በመነጨ ነው። የበሌላ-እጅ-ኖዋሪ ህግ የሚገነባው ደግሞ በህይወት ለመቆየት ከማያስችል አእምሮ በሚፈልቁ ፍላጎቶች ላይ ነው። ግለ-ነፃነት ካለው ኢጎ የሚመነጭ ሁሉ በጎ ነው። በሌላ ጥገኛ ከመሆን የሚመነጭ ሁሉ ደግሞ ክፉ ነው።

በትክክለኛ ትርጉሙ ራስወዳድ ሰው ሌሎችን ለራሱ ጥቅም ብሎ መስዋእት የሚያደርግ አይደለም። ይልቅ ሌሎችን እንደ መጠቀሚያ ከመውሰድ ፍላጎት በላይ ከፍ ብሎ ባለ ነገር ላይ የቆመ ነው። በነሱ አማካኝነት አይደለም ነገሮችን የሚከውነው። በግቡ፣ በመነሾ ምክንያቱ፣ በሃሳቡ፣ በምኞቱ፣ በኤነርጂ ምንጩ ላይ ተቀዳሚ ጉዳዩ ሌሎች አይደሉም። ለሌላ ሰው ሲል አይኖርም፤ ሌሎችም ለርሱ ሲሉ እንዲኖሩ አይጠይቅም። በሰዎች መካከል የወንድማማችነት እና የእርስበርስ መከባበር እውን የሚያደርገው ቅርፅ የሄው ነው።

የሰዎች የችሎታ ደረጃ ቢለያይም፣ መሰረታዊው መርህ ግን አይቀየርም። የግለ-ነፃነቱ ደረጃ፣ ተነሳሽነቱ እና ለስራው ያለው ፍቅር፣ የአንድን ሰው የስራ ተሰጥኦ እና የሰብእናው ምንነት ይወስናሉ። የሰውን ምግባረ-እሴት እና ዋጋ (ወይም ቫልዩ) ብቸኛ መለኪያ ግለ-ነፃነት ነው። ሰው ለራሱ የሆነውን እና ራሱን የቀረፀበትን እንጂ ለሌሎች በሰራው ወይም ባልሰራው ነገር አይደለም የሚለካው። የሰብእና ክብርን (personal dignity) የሚተካ ምንም ነገር የለም። ከግለ-ነፃነት ውጪ ደግሞ የሰብእና ክብር መለኪያ ስታንዳርድ የለም።

ትክክለኛ በሆኑ ዝምድናዎች ሁሉ አንዱ ለሌላው መስዋእት የሚያደርግበት ነገር አይኖርም። አንድ አርክቴክት ደንበኞች ያስፈልጉታል፤ ስራውን ግን ለነሱ ምኞት አሳልፎ አይሰጥም። ለነሱም አርክቴክቱ ያስፈልጋቸዋል፣ ግን ደግሞ መክፈል ስለሚችሉ ብቻ ህንፃን ማዘዝ አይችሉም። ሰዎች የስራ ፍሬአቸውን የሚለዋወጡት ፍላጎቶቻቸው ሲጣጣሙና ግብይቱንም ሲፈልጉት ሆኖ ነፃ፣ የጋራን ጥቅም፣ እና የጋራ መፈቃቀድ ላይ ተመስርተው ነው። ካልፈለጉ ግብይቱን እንዲያከናውኑ አይገደዱም። ሌላ ወደ መፈለግ ይሄዳሉ። እኩልነት ባላቸው ሰዎች መካከል ሊኖር የሚችል ብቸኛ የትስስር ቅርፅ ይሄው ነው። ከዚህ ውጪ የሆነ ዝምድና የጌታ እና የባርያ ውይም ደግሞ የገዳይ እና የሙዋች ዝምድና ነው የሚሆነው።

በብዙሃን ውሳኔ በኮሚቴ ተኩኖ የተሰራ ስራ የለም። ሁሉም የፈጠራ ስራ በአንድ ግለሰብ ሃሳብ መሪነት ነው ከግብ የሚደርሰው። አንድ አርክቴክት ህንፃውን ለመገንባት ብዙ ሰዎች ያሰፈልጉታል። ዲዛይኑን ግን በድምፅ ብልጫ እንዲያፀድቁለት አይጠይቃቸውም። በነፃ ስምምነት አብረው ይሰራሉ። እያንዳንዱም ነፃ ሆኖ በተገቢ ቦታው ስራውን ያከናውናል። አንድ አርክቴክት በሌሎች የሚመረቱ እንደ ብረት፣ መስታዎት፣ ኮንክሪት የመሳሰሉትን ይጠቀማል። ሆኖም ግን እነዚህ ማቴሪያሎች የአርክቴክቱ እጅ እስኪያርፍባቸው ድረስ ያው ብረት፣መስታዎት፣ እና ኮንክሪት እንደሆኑ ይቆያሉ። እነዚህ ነገሮች ላይ እሱ የሚሰራው ስራ የራሱ ምርት እና የራሱ ንብረት ይሆናል። በሰዎች መካከል አብሮ ለመስራት የሚያስችል በቸኛው መንገድ ይሄው ነው።

በዚህ ምድር የመጀመሪያው መብት የኢጎ መብት ነው። የሰው ተቀዳሚ ግዴታም ለራስነቱ ነው። ሞራል ህግጋቱ አድርጎ መያዝ ያለበትም፣ ዋና ዓላማውን በሌሎች ሰዎች ጥገኝነት ውስጥ ፈፅሞ ማስቀመጥ እንደሌለበት ነው። የሞራል ግዴታው አድርጎ መውሰድ ያለበት ደግሞ፣ ተምኔቱ በሌሎች ሰዎች ጥገኝነት ስር እስካልሆነ ድረስ የተመኘውን እንዲፈፅም ነው። ይሄ በፈጠራ ፋኩልቲው፣ በሃሳቡ፣ እና በስራው ዙሪያ ያሉትን በሙሉ የሚያጠቃልል ነው። በወሮበላ፣ በሌላ-እጅ-ኖዋሪ፣ እና በአንባገነን ዙሪያ ያሉትን ግን አያጠቃልልም።

አንድ ሰው ሲያስብም ሆነ ሲሰራ ብቻውን ነው። ብቻውን መዝረፍ፣ መጨቆን፣ ወይም መግዛት ግን አይችልም። ዝርፊያ፣ ጭቆና፣ እና መግዛት እንዲኖሩ ተበዳዮች መኖር አለባቸው። በሌሎች ላይ ጥገኛ መሆንን ያመለክታሉ። እነዚህ በሙሉ የ በሌላ-እጅ-ኖዋሪ ተግባራት ናቸው።

ገዚዎች ራስወዳዶች (egoist) አይደሉም። ምንም ነገር መፍጠር አይችሉምና። የሚኖሩት በሌሎች ሰዎች ድጋፍ አማካኝነት ነው። አላማቸውም ዜጎችን በባርነት ማስገበር ነው። ልክ እንደ ለማኝ፣ ማህበራዊ አገልጋይ (social worker)፣ እና ሽፍታ የጥገኝነቱ አይነት ቢለያይ ነው እንጂ በሌሎች ጥገኝነት ላይ ነው የሚኖሩት።

ሰዎች ለዘመናት የተሰበኩት ግን ጨቋዋኞች፣ አጼዎች፣ አንባገነኖች የሚሆኑ በሌላ-እጅ-ኖዋሪዎችን የራስወዳድነት ምሳሌ አድርጎ እንዲያዩዋቸው ነው። በዚህ የተጭበረበረ ሃሳብ ምክንያትም ሰዎች ኢጎአቸውን፣ ራስነታቸውን እና ሌሎችን እንዲጥሉ እንዲያስወግዱ ተደረጉ። የማጭበርበሪያ ሃሳቡ ባለ-ፈጠራዎችን ለማጥፋት ወይም ደግሞ ለመግራት ያለመ ነው። ከባለ-ፈጠራ ሰው አንፃር ሲታይ ደግሞ ማጥፋትም መግራትም ያው አንድ ናቸው።

ከታሪክ መጀመሪያ ጀምሮ ሁለቱ ተቀናቃኞች ፊት ለፊት ተፋጠው እንደቆሙ ናቸው። ባለ-ፈጠራ ሰው እና በሌላ-እጅ-ኖዋሪው። የመጀመሪያው ባለ-ፈጠራ ሰው ተሸከርካሪን ሲያስገኝ፤ በሌላ-እጅ-ኖዋሪው የመለሰው ለሌላ-ቅድሚያነትን በማስገኘት ነበር።

ባለ-ፈጠራው ሰው- ክልከላ ቢደረግበት፣ ተቃውሞ ቢደርስበት፣ ቢከሰስ፣ ቢጨቆን- ይሄን ሁሉ ችሎ የሰውን ልጅ በጫንቃው ተሸክሞ ቀጠለ፣ ወደፊት ተራመደ። በሌላ-እጅ-ኖዋሪው እነዛን እንቅፋቶች ከማስቀመጥ ውጪ ያበረከተው ነገር የለም። ይሄ ፍልሚያ ሌላ ስም አለው፤ ግለሰብ(Individual) ከ ጋርዮሽ(Collective) የሚያደርገው ፍልሚያ።

በጋርዮሽ ማህበረሰብ "የጋራ-ጥቅም" (Common-Good) የሚባሉት ዘር፣ መደብ(class)፣ ሀገር ወዘተ በሰው ልጅ ጫንቃ ላይ ለተገነቡ ሁሉም ዓይነት ጭቆናዎች የሚቀርቡ መደለያ ምክንያቶች ናቸው። አብዘኛው የታሪክ አሰቃቂ ኩነቶች የተፈፀመው ለሌላ-ቅድሚያ በሚል መርህ ስም ነው። በታሪክ የራስወዳድነት ድርጊት ከ በየሌላ-ቅድሚያነት ሃዋርያት የደረሰው እልቂት ጋር ሲነፃፀር የሚወዳደር ነው? ችግሩስ የሰዎች ግብዝነትን ነው የሚያሳየው ወይስ የመርሁ ባህርይ? ሀሌም አስከፊ ግድያ የሚፈፅሙት ቅን የየሌላ-ቅድሚያነት ተከታዮች ነበሩ። እንከን-የለሽ ማህበራዊ ስርዓት ላይ መድረስ የሚቻለው አንገት መቅሊያ (guillotine) እና ተኩዋሽ ቡድንን በመያዝ ነው ብለው ያምኑ ነበር። የመግደል መብታቸው ላይ ጥያቄ ያነሳ አንድም አልነበረም፤ ምክንያቱም ለሌሎች ሲሉ ነዋ የሚገድሉት። አንድ ሰው ለሌሎች መስዋእት መሆን እንደሚገባ አስቀድመው የተቀበሉት ጉዳይ ነውና። ገዳዮቹ ይቀያየራሉ የትራጀዲው መንገድ ግን አንድ አይነት ነው። **ለሰው ልጅ በሙሉ ፍቅርን በማወጅ የጀመረው በጎ-አድራጊ (Humanitarian) እጁ በደም ባህር ውስጥ ነክሮ ይጨርሳል። ይሄ ጉዳይ አሁንም እየቀጠለ ነው፤ ሰዎች ጥሩ ተግባር ብለው የሚቀበሉት ራስወዳድ ያልሆነውን ነገር እስከሆነ ድረስ ደግሞ ወደፊትም ይቀጥላል።** ይህ ደግሞ የሌላ-ቅድሚያነት ሰባኪው በለመደው በዚሁ መንገድ እንዲቀጥል እና መከራውን ተበዳዮቹ ላይ በመጫን እንዲሸከሙት ያስችለዋል። ሁሌም የጋርዮሽ መሪዎች ለራሳቸው የሚሆን የኔ የሚሉት ነገር የላቸውም፤ ውጤቱ ግን ማስተዋል ይቻላል።

ሰዎች እርስበርሳቸው ሊያደርጉት የሚችሉ ብቸኛው በጎ ነገር እና የዝምድናቸው ትክክለኛ መገለጫ መሆን ያለበት "እጅህን ከኔ ላይ አንሳ!" ነው። Hands off!

አሁን በግለሰባዊነት መርህ የታነፀ ማህበረሰብ ውጤት ደግሞ ተመልከቱ- ይቺ አገራችን [አሜሪካ]። በታሪክ ከተከሰቱ አገራት በሙሉ የላቀች። የታላቅ ስራ፣ የታላቅ ብልፅግና፣ የታላቅ ነፃነት አገር። **ይቺ አገር በራስ-አልባ አገልግሎት፣ በመስዋእት፣ አሳልፎ በመስጠት፣ ወይም ደግሞ በሌላ ማንኛውም የሌላ-ቅድሚያነት እሳቤ ላይ አልታነፀችም። የሰው ልጅ በዚህ ምድር ላይ ደስታ የሚያጎናፅፈውን መንገድ እንዲከተል የሚያስችል የግለሰብ መብት መሰረት ላይ ነው የታነፀችው። የሌላን ደስታ አይደለም፤ የራሱ የግለሰቡ ደስታ። የራሱ የሆነ፣ ግላዊ፣ ራስወዳድ ምክንያት ያለው። ውጤቶቹን ተመልከቱ። በህሊናችሁ መነፅር ገምግሙ።**

ግጭቱ ከጥንት ጀምሮ የነበረ ነው። ሰዎች ወደ እውነታው ተቃርበው ነበር፤ ሆኖም ግን በየጊዜው አንዱ ስልጣኔ ሲወድቅ ሌላው ይከተላል። ስልጣኔ ማለት ማህበረሰብ ከተቡዋድኖ ኑሮ ወደ ግላዊ ኑሮ የሚያደርገው ጉዞ ነው። ከጫካ ኑሮ ያልወጣ ሰው ኑሮው በጎሳ ህግ የሚመራ የአደባባይ ኑሮ ነው። ስልጣኔ ማለት ሰውን ከሰዎች ነፃ የሚያወጣ ሂደት ነው።...

<ትእምርተ ጥቅስ ተዘጋ>

አሁንም እንግዲህ በዚህ በግለሰባዊነት አውድ ውስጥ ሆነን ስንመለከትው "በተዋህዶ ከበረ" የተጠቃሚነት እሴት ይጎድለዋል የተባለው በተአምራታዊነት እና በብህትውና ላይ የተመሰረተው ያሬዳዊው ስልጣኔን ከ ምእራባዊው ሳይንስ እና ቴክኖሎጂን ማፃመር መሆን እንደሌለበትነው። ይሄ ዓይነት በተዋህዶ ከበረ አሁንም መከሸፍ አለበት።

ይልቅ እኔ መሆን ያለበት የምለው፣ አይን ራንድ "ሰውን ከሰዎች ነፃ የሚያወጣ ሂደት" ያለችውን የስልጣኔ ፍቺ የጎደለውን እና ተዳፍኖ ያለውን (የብርሃን ጨረሩ ግን ጨርሶ ያልሞተውን) ቅድመ-ክርስትና አክሱም የነበረውን እና ከአትናትዮሳዊ ክርስትና በሁዋላ ደግሞ ዶግማውን በመቃወም በየጊዜው በተነሱ ግለሰባዊት ነፍስ በነበረቻቸው ስማቸውን ማወቅ በልቻልናቸው ግለሰቦች አማካኝነት ብልጭ ድርግም እያለ በእነ ደቂቀ እስጢፋኖስ፣ ፈላስፋው ዘርአ የእቆብ፣ ነጋ ድራስ ገብረሂወት ባይከዳኝ፣ ሀዲስ አለማየሁ፣ በአሉ ግርማ፣ እጉዋለ ገብረ ዮሃንስንም ራሱ እና ሌሎች ግለሰቦችን አልፎ እኛ ላይ የደረሰውን አክሱማዊውን መንፈስ እና ምእራባዊውን ግለሰባዊነት ነው መሆን ያለበት።

በሚቀጥለው ክፍል ይሄንን የሚደግፉ የሃሳብ እርሾዎች የእጉዋለ የከፍተኛ ትምህርት ዘይቤ መፅሀፍ ላይ መኖራቸውን እንዳስሳለን።

ሰላም

በምስራቅ አፍሪካ ዳርቻ ሰማይ ላይ(የመጨረሻው ክፍል)

የእጉዋለ ገብረዮሀንስ የፍልስፍና መንገድ

ባለፉት ክፍሎች የእጉዋለ በተዋህዶ ከበረ ፕሮጀክት ለምን እንደከሸፈ ወይም ደግሞ መክሸፍ እንደነበረበት ተመልክተናል። አሁን የቀረው የእጉዋለ በተዋህዶ ከበረ ፕሮጀክት ሀሳብ ብቻ ነው የከሸፈው ወይስ ፍልስፍናውም ጭምር የሚል ጥያቄ ነው። ለመሆኑ የእጉዋለ ፍልስፍና ወይም ደግሞ ፍልስፍናዊ አበርክቶስ ምንድን ነው? የሚል ጥያቄም በተደጋጋሚ ይነሳል። በዚህኛው ክፍል የእጉዋለን የፍልስፍና መንገድ በመመልከት “በምስራቅ አፍሪካ ዳርቻ ሰማይ ላይ” የሚለውንም ጭብጥ እንቁዋጨዋለን።

መግቢያ

እጉዋለ የከፍተኛ ትምህርት ዘይቤ ሀሳብ እንዲያመጣ እና የ ”በተዋህዶ ከበረ” መፍትሄ እንዲያፈልቅ መግፍኤ-ምክንያቱ ምን ነበር?

በ 20ኛው ክዘ መጀመሪያ አካባቢ በተለይም ደግሞ ሃይለስላሴ ወደ ሥልጣን ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ ብዙ ኢትዮጵያውያን በትምህርትም ይሁን በመንግሥት ሥራ ምክንያት ውጭ አገር ሄደው ምዕራባዊውን የሥልጣኔ ዕድገት እና የኑሮ ዘይቤ መመልከት ችለዋል። ታዲያ እዛ ሄደው የታዘቡትን የዕድገት፣ የብልጽግና፣ የዘመናዊነት እና በአጠቃላይ የስልጣኔው ገጽታ በአገራቸው ካለው ሁኔታ ጋር ሲያነፃፅሩት የመሬት እና የሰማይ ያክል መራራቅ እንዳለ ተገነዘቡ። በዚህም ምክንያት ብዙዎቹ በጥልቅ ሃዘን ሆነው በቁጭት ተብሰልስለዋል።

አብዛኞቹ የምዕራቡ ዓለም አገራት ከመፈጠራቸው በፊት ብቻ ሳይሆን ሊታሰቡ እንኩዋ በማይችሉበት ዘመናት የዓለም ቁንጮ መሆን የሚያስችል የስልጣኔን መንገድ ጀምራ የነበረች አገር፣ በምን ምክንያት የሁዋላ ቀርነት እና የድንቁርና መናህሪያ ልትሆን እንደቻለች መረዳት ከብዶአቸዋል።

**በዳኛቸው ወርቁ አገላለፅ (አደፍርስ ልብ ወለድ መጽሐፍ) ያቺ በምዕራቡ ዓለም "የምትጣደፈው፣ የምትፍለቀለቀው፣ የምትንቦለቦለው ሕይወት"፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ምንም የጎደላት ነገር የሌለ ይመስል እፎይ ብላ በእርጋታ ታምማለች፣"በተገማሸረ መስክ ውስጥ እንደሚብሰከሰክ ውሃ... ልደታ፣ አባ ጉባ፣ በዓታ፣ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጉዋድ፣ አቡየ ጻድቁ፣ መስቀለ ኢየሱስ፣ ቅድስት ሃና፣ ቅዱስ ሚካኤል፣ እስጢፋኖስ ቀዳሜ ሰማዕት፣ ቅዱስ ማርቆስ፣ ቅዱስ ዮሐንስ፣ ደመራ መስቀል፣ ገና፣ ጥምቀት፣ ፋሲካ...ትፈስሳለች ታምማለች።" በምዕራቡ ዓለም በሰማይ ጠቀስ ፎቆች፣ በሰፋፊ መንገዶች፣ በትላልቅ አውሮፕላኖች እና አውሮፕላን ማረፊያዎች፣ በዘመናዊ መኪኖች፣ በዘመናዊ አልባሳት፣ በግል እና በአካባቢ ንጽህና፣ ሌሊቱን ከቀን ብርሃን መለየት በሚያዳግቱ የኤሌክትሪክ ብርሃናት፣ በሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ፈጠራዎች፣ በቴያትሮች እና ፊልሞች፣ በሙዚቃ እና ስነጽሁፎች፣ በግለሰብ ነፃነት ላይ የተመሰረተ ዴሞክራሲያዊ የመንግሥት አስተዳደር እና ተቋማቶች... ወዘተ "የምትጣደፈው የምትፍለቀለቀው የምትምቦለቦለው ይቺው ሕይወት"፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ግን፣ "በመውቃት፣ በመከመር፣ በማጭድ፣ በማረም፣ በመቆፈር፣ በመጎልጎል፣ በመተለም፣ በማረስ... ከብት በማሰማራት፣ በማስገባት፣ እንጨት በመልቀም፣... በፋሲካ፣ በፍልሰታ፣ በገሃድ፣ በነነዌ፣ በሁዳዴ፣ በጾመ ሐዋርያት፣ በዓርብ ሮብ፣ ትደለላለች ትደክማለች።... ኤዛና፣ አምደጽዮን፣ ዘርአያዕቆብ፣ ሱስንዮስ፣ አምሃየስ፣ አብዬ መሳፍንት፣ ቴድሮስ፣ ዮሐንስ ምኒልክ፣ ደለልዋን ትተዋለች። አዝብጤ፣ ጫልቱ፣ ላጲሶ፣ ጎንጫ፣ ሓዳስ፣ ቀመሩ፣ አዛለች፣ ወርዶፋ፣ አርያም፣ አያንቱ፣ ጨቡዴ፣ ገብሬ፣ ተዋበች፣ ነስሩ፣ መገርቱ፣ ለተሚካኤል፣ እርገጤ፣ ቢራቱ፣ ሐጎስ፤ ኩሬ፣ ክትር፣ ጉለንታ፣ መስኖ በእርጋታ በዝግታ ትፈስሳለች- በሌላ አገር የምትጣደፈው የምትፍለቀለቀው የምትምቦለቦለው ይቺው ሕይወት..."

ይሄን የምዕራቡን የሥልጣኔ ዕድገት ርቀት ተመልክተው፣ ስለ አገራቸው ኢትዮጵያ ሁኔታ በቁጭት የተንገበገቡት የያንጊዜው አብዛኞቹ ተማሪዎች እና የተወሰኑ ባለሥልጣናት፣ አገራቸው ገብተው ምን ቢያደርጉ እንደሚበጅ የሚጠቁም መፍትሔ ለማግኘት በጋራ ምክክርም በየፊናቸውም ከመብሰልሰል አልቦዘኑም። ቀስበቀስም ኢትዮጵያን ለሁዋላ ቀርነት እና ድንቁርና የዳረጋት “ዘመናዊ ትምህርት ማግኘት አለመቻልዋ ነው” የሚል ሃሳብ ቅርጽ እየያዘ፣ በአመዛኙም በሁሉም ዘንድ ተቀባይነትም እያገኘ መጣ። ዘመናዊ ትምህርትን እንደ ቁልፍ መፍትሔ አድርገው ሲወስዱት በመካከላቸው ብዙ ቅራኔ ያልነበረ ቢሆንም ቅሉ፤ ይሄ ዘመናዊ ትምህርት በምን አይነት መንገድ ነው ኢትዮጵያ ውስጥ መትከል የሚቻለው የሚል ጥያቄ መመለስ ግድ ሲሆን ግን ወደ ሁለት ጐራ እንዲከፈሉ ሆነዋል።

አንደኛው ወገን፣በፍጥነት የምዕራቡን ዓለም የሥልጣኔ ዕድገት ደረጃ መድረስ የሚቻለው፣ ያረጀ ያፈጀውን ጥንታዊው የኢትዮጵያ ሥርዓተ ማህበር፣ ባህል፣ እና ትውፊት ተነቅሎ በዘመናዊ ትምህርት አማካኝነት ምዕራባዊውን የሥልጣኔ ዘይቤ መተካት አለበት የሚል ሥርነቀል (Radical) አስተሳሰብ የያዙትን ያጠቃለለ ነው። ሌላኛው ወገን ደግሞ አንድ ማህበረሰብ ለዘመናት የተቃኘበትን ሥርዓት፣ ባህል፣ እና ትውፊት ለመንቀል መሞከር ትክክል አይደለም፤ መነቀል ያለበት ነገር ካለ ደግሞ በአንድ ጀምበር ነቅሎ መጣል አይቻልም፤ ስለዚህ መደረግ ያለበት ነባሩን ሥርዓት በማይጎዳ መልኩ ዘመናዊውን ትምህርት ማስተዋወቅ የሚል ወግ አጥባቂ (Conservative) ሃሳብ የያዙትን ያጠቃልላል።

በዚያን ጊዜ የነበሩት ባለሥልጣናት፣ መኩዋንኑቱ እና መሳፍንቱ፣ ንጉሥ ሃይለስላሴም ጭምር ዘመናዊው የኑሮ ዘይቤ አገራቸው ላይ በፍጥነት እንዲስፋፋ ከመመኘት የተነሳ እና፣ "ሕዝቡን መርተው ወደ ዘመናዊነት እንዲሸጋገር ያደረጉ"፣ የሚል ስም ለማትረፍ ካላቸው ጉጉት የተነሳ፣ ንጉሣዊውን አስተዳደር ሳይነካ ሌላው ነገር ግን በአመዛኙ የሥርነቀሉ ወገን ሃሳብ በመውሰድ ለውጥ (reform) ለማምጣት ተሞከረ። በዚህም ደሞዝ የሚከፈለው ዘመናዊ ጦር ግንባታ ተካሂዶአል፣ የመንግሥት አስተዳደራዊ መዋቅር ተቀይሮአል፣ በተለያዩ የአገሪቱ ከተሞች ትምህርት ቤቶች እንዲከፈቱ ተደርጐአል...ወዘተ። እዚህ ላይ ግን አንድ ችግር ተከሰተ። ችግሩን ሀዲስ አለማየሁ በወንጀለኛው ዳኛ ልብወለድ መጽሐፋቸው መግቢያ ላይ እንደሚከተለው አብራርተውታል። እላይ ከተገለጹት ነገሮች በተጨማሪ፣

"የሕግ፣ የፍርድ ስነስርዓት፣ እና እንደነሱ ያሉ የኢትዮጵያን ሕዝብ ኑሮ የሚነኩ ስርዓቶች ተጨምረውበት፣ የቆየው የኢትዮጵያ የኑሮ ሥርዓት ከስር እንዳለ፣ ይህ የፈረንጆች እንግዳ ሥርዓት ባዋጅ በላዩ ተጫነበት። ነገር ግን እንግዳው ሥርዓት ለጠቅላላው ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ለባለሥልጣኖች እና ለዬስራው ክፍል መሪዎች ጭምር ባዕድ ስለነበረ በሥራ ላይ ማዋሉ ቀላል አልነበረም። ስለዚህ ወጣቶች ከዘመናውያን ትምህርትቤቶች እየተማሩ እስኪወጡ ድረስ፣ በጥንታዊው ያስተሳሰብና ያሰራር ልማድ ሲሰሩ የኖሩት የፍርድ ይሁን ያስተዳደር ባለሥልጣኖች፣ በዚያው በኖሩበት ያስተሳሰብ እና ያሰራር ልማድ መቀጠሉ ይቀናቸው ስለነበረ ባዕዱ ሥርዓት በሕግ የታወቀውን ያክል በግብር ይታወቅ ነበር ለማለት አያስደፍርም።"

"ወጣቶች ከውጭ አገርና ከኢትዮጵያ ዘመናውያን ትምህርትቤቶች እየተማሩ መውጣት ከጀመሩ በሁዋላ እንኩዋ ካዲስ አበባና ካንዳንድ ከተሞች ተርፈው በየሥራው ክፍል ሰፊውን ገጠር ለማዳረስ ሊበቁ አልቻሉም። በየገቡበት ስራም ቢሆን በስልጣን ላይ ከቆዩት ጥንታውያን ያስተዳደርና የፍርድ ባለሥልጣኖች ስር መስራት ስለነበረባቸውና በሁለቱ ወገኖች መህከል አለመግባባት ስለ ነበረ የኢትዮጵያ የልማት እርምጃ ተሰፋ እንደ ተደረገው ሊፋጠን አልቻለም።"

እዚህ ላይ ወግ አጥባቂዎቹ ድሮውም እኮ ሥርነቀል አካሄድ አያወጣም ብለን ተናግረን ነበረ እኮ፤ አሁንም ቢሆን መንገዱን ለኛ ልቀቁልን ማለት ጀመሩ። ሥርነቀልነት አራማጆቹ ደግሞ የተማረው ሃይል እንቅፋት፣ ችግር፣ መከራ ቢያጋጥመው እንኩዋ እነዚህን ተቁዋቁሞ ራሱን ለሌሎች አሳልፎ መስዋዕት አድርጎ ማቅረብ ባለመቻሉ እንጂ ለውጥ ማምጣት ይቻል ነበር ብለው ተከራከሩ።እንዲህ እንዲያ እያሉ እርስበርሳቸው ቢነታረኩም ሁለቱም ወወገኖች ችግሩን ከራሳቸው ህሊና የሚመነጭ መፍትሄ በማምጣት ሊፈቱት እንደማይችሉ በደንብ ተገንዝበውታል። **በዚህ ጊዜ ተዲያ ሁለቱም ወገኖች አንድ ዘዴ ላይ እኩል አነጣጠሩ- ከሌሎች አገሮች ተሞክሮ መቅሰም።**

እዚህ ላይ ወግ አጥባቂዎቹ ፊታቸውን ወደ ጃፓን፣ እንግሊዝ ፣ፈረንሳይ የመሳሰሉት አዙረው፣ "ኢትዮጵያ እና ምዕራባዊ ሥልጣኔ"፣ "ጃፓን እንዴት ስለጠነች"፣ ወዘተ እያሉ ሲኩዋትኑ፤ ሥርነቀሎቹ ደግሞ ፊታቸውን በዋናነት ወደ ሩሲያ እና ቻይና አዞሩና **"ዲያሌክቲካዊ ቁስ-አካላዊነት"፣ "የአርሶ አደሮች አብዮት"፣ "የወዛደሮች አብዮት"፣**

አብዮት! አብዮት! አብዮት!... ድው፣ ኩዋ፣ ድው፣ ...ድው፣ ኩዋ፣... አብዮታዊት ኢትዮጵያ! ... ኩዋ፣ ኩዋ ኩዋ፣ ኩዋ፣ድም፣ ኩዋ፣ ድም...ኩዋ፣ ድም፣... አብዮታዊ ዴሞክራሲ! ሆሆሆ... ቡፍፍፍ... አብዮት ዘኢይበቁዕ አብዮት!

ይሄ ከሌሎች አገሮች ተሞክሮ መቅሰም የሚባል ሃሳብ ላይላዩን ሲያዩት በጎ ሃሳብ ቢመስልም ውስጡ ግን ለ በሌላ-እጅ-ኑዋሪነት(second-handedness) የሚያጋልጥ ክፉ መንፈስ በውስጡ ተሸክሞአል። ለዚህ ሁነኛ ማስረጃዬ ኢትዮጵያ ራስዋ ናት። **ይህንን "ከሌሎች አገሮች ተሞክሮ በመቅሰም የራስን ችግር ለመፍታት በሚያስችል መልኩ ማጣጣም (ማጣመም?)" ወይም በዘመኑ ቁዋንቁዋ "ካስተማይዝ" (customize) ማድረግ የሚል የሰነፎች (ወይም የፖለቲከኞች) መርህ ከተተከለ አንስቶ፣ ይሄውና በሶስቱም የአገዛዝ ስርዓቶች እየተተገበረ ከግማሽ ክፍለዘመን በላይ ቢያስቆጥርም፣ ተሞክሮ ተቀስሞባቸዋል ከሚባሉት አገሮች አንፃር ስትታይ ኢትዮጵያ እዚህ ግባ የሚባል ለውጥ ሳታመጣ እስከዛሬ ባለችበት እንደረገጠች ነው።**

አንድ ሰው ግን ከሁለቱ ጎራዎች የተለየ እና አዲስ መንገድ ይዞ ብቅ ብሎ ነበር። ዘመናዊውን የምዕራብ ሥልጣኔ እና ጥንታዊውን የኢትዮጵያ የኑሮ ሥርዓት ማስታረቅ ይቻል እንደሆነ ለማወቅ ከፈለግን ምርመራችንን መጀመር ያለብን ቅርንጫፎች ወይም ግንዶች ከሆኑት ፖለቲካዊ እና ባህላዊ እሳቤዎች ላይ ሳይሆን፤ ጠለቅ ብለን ከስረ መሰረታቸው ፍልስፍናዊ መነሻዎቻቸው ላይ መሆን ይኖርበታል የሚል አማራጭ ሃሳብ ነበር ይዞ የመጣው። ይህ ሰው ሊቁ ፈላስፋ አጉዋለ ገብረዮሐንስ ነው።

እጉዋለን ከወግ አጥባቂዎቹ እና ከስርነቀልተኞቹ ለየት የሚያደርገው “በተወህዶ ከበረ” ብሎ ባመጣው መፍትሄ ሃሳብ ሳይሆን የመፍትሄ ሃሳቡ ላይ ለመድረስ የተከተለው የፍልስፍና መንገድ ነው። በዚህም ሁለት አበይት ሀሳቦችን ማስተዋወቅ ችሎ ነበር። አንደኛው ትልቅ ማህበራዊ ቀውስ በሚያጋጥምበት ጊዜ አልታረቅ ያሉ ሃሳቦችን ለመመርመር የሚረዳ የተጠየቅ ዘዴ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ይህንን የምርመራ ዘዴ “በየጊዜው እያደገ በሚሄድ እውቀት” ለመቃኘት የሚያስችለውን የትምህርት ዘይቤ ፅንሰ ሀሳብን (ወይም የትምህርት ፍልስፍናን) ሁሉን አቀፍ(universal) በሆነ መሰረት ላይ አስቀምጦታል። አሁን ሁለቱን የእጉዋለ አበርክቶዎች በዝርዝር እንመልከት።

1. ታሪክ-ፍልስፍና: ፍልስፍናዊ የተጠየቅ ምርመራ በማድረግ መፍትሄ የማፈላለግ ዘዴ

እጉዋለ እነዛ ስርነቀልተኞች እና ወግ አጥባቂዎቹ ጎራዎች ከሚከተሉት መንገድ ተለይቶ ወጥቶ ለምን የፍልስፍና መንገድን መከተል እንደመረጠ በደንብ ዘርዘር አድርጎ የሰጠው ማብራሪያ የለም። ነገር ግን የከፍተኛ ትምህርት ዘይቤ መፅሃፉን የፃፈው ፍልስፍናዊ የተጠየቅ ምርመራ ዘዴ ተከትሎ እንደሆነ ግን በግላጭ ከመፅሃፉ የምናገኘው ጎልቶ የሚነበብ መንፈስ ነው። ይህች በገፅ ብዛትዋ ትንሽዬ የሆነች መፅሃፉ ጠንካራ ይዘት ሊኖራት የቻለውም፣ በአለም ላይ የነበሩ የወቅቱ ፈላስፎች ሳይቀሩ፣ ፍልስፍና ከሰዎች የእለት ተእለት ኑሮ ጋር ምንም ዓይነት ዝምድና የለውም እያሉ በሚሰብኩበት ወቅት የፍልስፍና ሃይል ምን ድረስ እንደሆነ በቀላል አማርኛ ማስረዳት መቻሉ ነው።

እጉዋለ ምእራባዊውን እና ኢትዮጵያዊውን የስልጣኔ ዘይቤ ማስታረቅ ይቻል እንደሆነ ለመመርመር እንዲረዳው የተጠቀመው ዘዴ ታሪክ-ፍልስፍናን (ወይም የፍልስፍና ታሪክን በእንግሊዘኛው History of Philosophy) እንደግብአት በመጠቀም የሆነ መደምደሚያ ላይ መድረስ መቻልን ነው። ይህ ዘዴ በኢትዮጵያ ታሪክ ከእጉዋለ በፊትም ሆነ ከእጉዋለ በሁዋላ ማንም ያልደፈረው አዲስ የምርመራ ስልት ነው።

ብዙዎች፣ ለታሪክ ኩነቶች መግፍኤ ምክንያት የሆኑ ሃሳቦችን ሳይሆን የታሪክ ኩነቶች ራሳቸውን ማለትም እገሌ በሆነ ዘመን እንዲህ አይነት ተግባር በመፈፀሙ ወይም ባለ መፈፀሙ፣ በሆነ ዘመን ላይ የታዩ እንደ ጦርነት፣ የኢንዱስትሪ ፋብሪካዎች መስፋፋት፣ የኪነ-ጥበብ ውጤቶች መብዛት አይነት ክስተቶች፣ ወዘተ እንደግብአት ተጠቅመው ተመራምረዋል። ለዚህም ነው ከሌሎች አገሮች እንኩዋ ተሞክሮ እንድንወስድ ሲመክሩን ጃፓን በዚህ ዓም በተከተለችው ፖሊሲ፣ ራሽያ በዚህ ሁኔታ በለኮሰችው አብዮት፣ እንግሊዝ በዚያ ሁኔታ በተከተለችው የኮንስቲትዩሽናል ሞናርኪ አስተዳደር...ወዘተ የሚሉ የአገራችንን አውድ እና ተሞክሮ የሚቀሰምባቸው አገራት አውድ በፍፁም ከግንዛቤ ሳይገባ፣ ኩነቶቹ “ቃል በቃል” እየገለበጡ የአገሪቱ ህግ ወይም ፖሊሲ ሆኖው እንዲፀኑ ሲያደርጉ የምንመለከተው።

ይሄ እጉዋለ አስተዋውቆን የነበረው ዘዴ ግን፣ ከሌሎች አገሮች ተሞክሮ መቅሰም ካስፈለገ እንኩዋን በየአገራቱ የተከናወኑትን የታሪክ ኩነቶችን ሳይሆን፣ የታሪክ ኩነቶቹ መግፍኤ-ምክንያት የሆኑትን ሃሳቦች እንደግብአት ወስዶ እጉዋለ እንደሚለው “መጀመሪያ የገዛ ራሳችንን ደህና አድርገን ማላመጥ መዋጥ፣ ቀጥሎም ከውጭ የመጣውን

በዚሁ መንገድ አሳልፎ” በጎ እና መጥፎ ገፅታቸውን መርምረን በመደባለቅና በማዋሀድ ለራሳችን ጥቅም የምናውልበት ተመራጭ መንገድ ነበር ያሳየን።

እዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባን ቁምነገር አለ። በክፍል ሁለት እና ከዚያም በሁዋላ እንደተመለከትነው ይሄን ዘዴ ተከትሎ የደረሰበትን የ“በተዋህዶ ከበረ” መደምደሚያ ሃሳብ ልክ አይደለም። ነገር ግን ይህ ማለት ስሁት ድምዳሜ ላይ ደረሰ ማለት እንጂ፤ የተከተለው ዘዴ ስሁት ነው ማለት እንዳልሆነ አሁን ግልፅ መሆን አለበት። ይህንን ጉዳይ በቀላል ምሳሌ እንመልከተው። አንድ ሰው የሚከተለውን መከራከሪያ ሃሳብ አቀረበ ብለን እናስብ፣

ሰው አራት አይኖች አሉት።

ሶቅራጥስ ሰው ነው።

ስለዚህ ሶቅራጥስ አራት አይኖች አሉት።

ሶቅራጥስ አራት አይኖች አልነበሩትም፤ ድምዳሜው ውሸት ነው። ሆኖም እዚህ ድምዳሜ ላይ የደረሰበት መንገድ ግን ትክክል ነው። ከተሳሳተ መነሻ በመነሳቱ ስሁት ድምዳሜ ላይ ደረሰ እንጂ የመከራከሪያ ዘዴው ግን ስሁት አይደለም። እጉዋለም ከተሳሳተ መነሻ ስለተነሳ ነው ከወግ አጥባቀዎቹ ብዙም ያልራቀ መደምደሚያ ላይ የደረሰው እላለሁ። የተሳሳቱ መነሻዎች የምላቸውም፣ አንደኛው ከአሪስቶትል እና ጆን ሎክ ይልቅ ወደ ፕሌቶ እና ካንት የፍልስፍና ስነስርዓቶች ማድላቱ፤ ሌላኛው ደግሞ የኢትዮያ የፍልስፍና ስርዓትን ድህረ ያሬድ ያለውን ብቻ በመውሰዱ ናቸው። እነዚህን ሃሳቦች በሌላ ጊዜ በሌላ ርእስ እመለስባቸዋለሁ።

ከላይ ከፍ ብዬ እንደጠቀስኩት እጉዋለ የታሪከ-ፍልስፍና ምንነት እና ጥቅም በግልፅ ሳያብራራልን ነው ወደ መፅሃፉ ጭብጦች የገባው። ነገር ግን የእጉዋለ አበርክቶዎች ግልፅ መሆን የሚችሉት ይሄ የታሪከ-ፍልስፍና ምንነት እና ጥቅም በትክክል ከተረዳነው በሁዋላ ስለሆነ፤ አሁን እኔ ከአብጀክቲቪዝም ፍልስፍና የሀሳብ ትምህርት ቤት(School of Thought) ተውሼ አብራራዋለሁ።የከፍተኛ ትምህርት ዘይቤ መፅሀፍ መቅድም ውስጥ መካተት የነበረበት ሀሳብ ተደርጎ መውሰድ ይቻላል። በዚህ መቅድምነት መፅሀፉ ቢነበብ የመፅሀፉን ጭብጦች በትክክል ለመረዳት አስተዋፅኦ ይኖረዋል የሚል ተስፋ አለኝ። የአብጀክቲቪዝም ፍልስፍናን የመረጥኩበት ምክንያት ደግሞ በአሁኑ ጊዜ ፍልስፍናን ፈላስፎች ወይም የፍልስፍና መምህራን ለግል ደስታቸው ብለው ትርጉም በሌላቸው ሀሳቦች እየተራቀቁ የሚዝናኑበት መስክ እና ከእለት ተእለት ኑሮ ጋር ደግሞ ፍፁም ግኙኝነት የሌለው ተደርጎ እንደሚሰበከው ሳይሆን፤ በግለሰብ ውስጥም ይሁን በማህበረሰባዊ ህይወት ውስጥ ወሳኝ ሚና ያለው እና ከእለት ተእለት ኑሮ ጋርም ጥብቅ ቁርኝት እንዳለው የሚያስተምር በዓለም ላይ ያለው ብቸኛው የፍልስፍና ትምህርት ቤት በመሆኑ ነው።

ብዙ ሰዎች ፍልስፍናን በትክክለኛ መገለጫው አያውቁትም። ፍልስፍና ህላዌን(Existence) እና ህይወትን የምንመለከትበት ሰፊ የእይታ አውድ ነው። ፍልስፍና የህላዌን፣ የእውቀትን፣ እና የእሴቶችን ባህሪያት የሚያጠና ነው። ከዚህ የተነሳም ፍልስፍና ቅርንጫፎች አሉት።

ስለ ህላዌ የሚያጠናው የፍልስፍና ቅርንጫፍ ዲበ-አካላዊነት(ወይም ሜታፊዚክስ) ይባላል። ሜታፊዚክስ የሁለንታ(Universe) ባህርይ በአጠቃላይ ይመረምራል። በምን ዓይነት ዓለም ውስጥ እየኖርን እንዳለን እና ልእለ-ተፈጥሮ (Supernatural) የሚባል ነገርስ ከዓለም ወድያንዲያ ሊኖር ይችላል ወይ? ስለሚሉ ጥያቄዎች የሚያብራራ ነው።

ስለ እውቀት የሚያጠናው የፍልስፍና ቅርንጫፍ ስነ-እውቀት(ወይም ኤፒስተሞሎጂ) ይባላል። ኤፒስተሞሎጂ፣ እውቀት የምናገኝበትን ትክክለኛው መንገድ ያጠናል። የትኞቹን የአእምሮ ተግባራት አካባቢያችንን ለመገንዘብ መጠቀም እንዳለብንና የትኞቹን ደግሞ ተገቢ ያልሆኑ ናቸው ብለን መተው እንደሚገባን የሚነግረን ነው። ከሁሉም በላይ ኤፒስተሞሎጂ የሚነግረን ነገር አመክንዮአዊ-አእምሮ(Reason) እውቀት የምናገኝበት ፋኩልቲ ከሆነ እንዴት እንደሚሰራ፤ ወይም ደግሞ ከአመክንዮአዊ-አእምሮ የተለየ ሌላ የእውቀት ማግኛ መንገድ ማለትም ጭፍን-እምነት (Faith)፣ ማህበረሰባዊ ደመነፍስ (Social Instinct)፣ ወይም የአንባገነን ገዢ ውቃቢ(The Dictator’s Feeling) የሚባል እንዳለ የሚነግረን ነው።

ስለ እሴቶች የሚያጠናው የፍልስፍና ቅርንጫፍ ግብረ-ገብነት(ኢቲክስ፣ ወይም ሞራሊቲ) ይባላል። ሞራሊቲ ከላይ በተጠቀሱት የፍልስፍና ቅርንጫፎች መሰረት ላይ የሚገነባ ነው። ማለትም ሰው ስለሚኖርበት ዓለም በሚኖረው እይታ ላይ እና የእውቀት ማግኛ መንገዶችን ጨምሮ ስለ ራሱ ተፈጥሮ የሚኖረው እይታ ላይ የሚገነባ ነው።

ሞራሊቲ የህይወት ትክክለኛ ዓላማ ምን እንደሆነ እና እንዴት ይሄን ዓላማ ማሳካት እንደሚቻል የሚነግረን ነው። ሞራሊቲ በጎ እና መጥፎ፣ ትክክል እና ስህተት፣ የሚፈለግ እና የማይፈለግ ለይተን ለመፍረድ ለመዳኘት የሚያገለግለንን መለኪያ(ወይም ስታንዳርድ) የሚሰጠን ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው የራሱን ደስታ የሚያሳካበትን መንገድ እንዲከተል ወይም ደግሞ ራሱን መስዋእት አድርጎ ለሌላ አካል ማለትም ለፈጣሪ ወይም ለጎረቤቱ እንዲያቀርብ የሚነግረው ሰውየው በውስጡ የተቀበለው ሞራሊቲ ነው።

ሞራሊቲን ለማህበራዊ ጥያቄዎች መልስ የሚጠቀመው የፍልስፍና ቅርንጫፍ ደግሞ ፖለቲካ (ወይም ፖለቲክስ) ይባላል። ፖለቲክስ ማህበረሰባዊ ስርዓቶችን እና ትክክለኛው የመንግሰት ሚና የሚያጠና ነው። ፖለቲክስ የፍልስፍናዊ ስርዓት ውጤት ነው እንጂ ራሱን ችሎ የቆመ ነገር አይደለም። በህላዌ፣ በእሴቶች፣ እና ለሰው ትክክለኛ የእውቀት ማግኛ መንገድ በሚሆን እይታ ላይ ተመርኩዘን ካልሆነ በስተቀር፣ በተፈጥሮአቸው የፖለቲካ ጥያቄዎችን ዝምብሎ በዘፈቀደ ማንሳት ወይም መመለስ የምንችላቸው አይደሉም።

ስለ ኪነ-ጥበብ (ወይም አርት) የሚያጠናው አምስተኛው እና የመጨረሻው የፍልስፍና ቅርንጫፍ ደግሞ ኤስቴቲክስ ይባላል። ኤስቴቲክስ፣ ኪነ-ጥበብ (አርት፣Art) ምንድን ነው? በሰው ህይወት ውስጥ ያለው ሚና ምንድን ነው? የአርት ስራዎችንስ በምን መለኪያ ነው የምንመዝናቸው? የሚሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል። እነዚህ ጥያቄዎችን ለመመለስ ደግሞ ወደ ሜታፊዚክስ ጠልቆ ይገባል። አርት ምክኑይ(rational) የሆነ፣ ዓለማዊ፣ እና ተግባራዊ ዓላማ አለው። አርት መሰረታዊ የሰው ልጅ ፍላጎትን የሚያረካ ነው። ይሄ ፍላጎትም ማቴሪያላዊ ሳይሆን መንፈሳዊ ፍላጎት ነው። **"አርት ከሰው ልጅ ህልውና ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው" ትላለች አይን ራንድ "ለአካላዊ ህልውናው ሳይሆን አካላዊ ህልውናው የሚመረኮዝበትን የንቃተህሊናው(Consciousness) ህልውና ተጠብቆ እንዲቆይ የሚያደርግ ነው።"**

ለአንድ ባህል ስለ ዓለም ሁኔታ ያለውን ርእዮት መጋቢው ፍልስፍና ነው። በኡብጀክቲቪዝም ፍልስፍና እይታ፣ ፍልስፍና በግለሰብ ሂወት ውስጥ ወሳኝ ድርሻ አለው። አንድ ግለሰብ በግልፅ አውቆትም ይሁን ሳያውቀው ሂዎቱን በፍልስፍና ነው የሚመራው። ልዩነቱ ሰዎች አዘጋጅተው የሰጡት እንደ ሃይማኖት ዓይነት ፍልስፍና ነው የያዘው ወይስ ራሱ መርምሮ ያገኘው ነው የሚል ነው። እናም ፍልስፍና በግለሰብ ሂዎት ውስጥ የሚጫወተው ትልቅ ሚና እንዳለው ሁሉ በአንድ አገር ታሪክም ፍልስፍና ጉልህ ድርሻ አለው። ፍልስፍና የአንድን ባህል ጉዞ እና ታሪክ፣ መሰረታዊ የእሴቶቹ ህግጋት፣ ከዚህ የተነሳም ሰዎች የመለኪያ እና የፖሊሲ ምርጫዎችንና ውሳኔዎችን የሚቀርፁበት አውድ ነው። ፍልስፍና የታሪክ ኩነቶችን መግፍኤ-ምክንያት፣ የሰዎች ጥንተ-መዘውር(Prime mover) ነው።

ፍልስፍናን በዚህ መንገድ መረዳት ከቻልን ታሪክ-ፍልስፍናን ለመረዳት ቀላል ይሆናል። ታሪክ-ፍልስፍና ሃሳቦች በታሪክ የነበራቸውን ሚና ምን እንደሆነ የሚያብራራ ነው። "ታሪክ-ፍልስፍና በዋናነት የሚያነሳቸው ጥያቄዎች" ይላል ሊዮናርድ ፒኮፍ(Leonard Peikoff) "ባለፉት ዘመናት ሰዎች ለምንድነው ተግባራቸውን በእንደዚያ ዓይነት መንገድ ሊከውኑ የቻሉት? በንዳንድ ባህሎች እና ዘመናት ላይ የታዩት ቁልፍ እድገቶች፣ መውደቅ መነሳቶች፣ የአዲስ አቅጣጫ ቅያሶች (turning points)፣ የመሳሰሉት ምክንያታቸው እና ትርጉማቸው ወይም ዓላማቸው ምንድን ነው? ይህን የሰዎችን የታሪክ ሂደት መግለፅ የሚችል ጥንተ-መዘውርስ (Prime mover) ምንድነው? የሚሉ ጥያቄዎችን ነው።"

ታሪክ-ፍልስፍናን የምናጠናበት ዋናው ዓላማም በአንድ ባህል የዕድገት ሂደት ላይ ያሉትን ኢኮኖሚያዊ፣ፖለቲካዊ፣ሃይማኖታዊ፣እና ኪነጥበባዊ የታሪክ ሁኔታዎችን ወደ ፍልስፍናዊ ምንጫቸው እንዲያደርሰን ነው። የምርመራው ግብ የተለያዩ የፍልስፍና ስርዓቶች መሠረታውያንን(fundamentals) በመለየት የትኞቹ ፈላስፎች የየትኛውን ባህል ፍልስፍናዊ አቅጣጫ መወሰን እንደቻሉ መለየት እንችላለን። ለምሳሌ እጉዋለ የተጠቃሚነት ደረጃ ይጎድለዋል ያለውን ኢትዮጵያዊው የፍልስፍና ሥርዓት ከለየ በሁዋላ ለዚህ ፍልስፍና ምንጭነት ወደ ያሬድ ይመዝዘዋል።

እጉዋለም በዚህ ዘዴ አማካኝነት የከፍተኛ ትምህርት ዘይቤን ሃሳብ ከታሪክ-ፍልስፍና ምርመራ አንፃር ሲያቀርብልን፣ በመጀመሪያ የምዕራቡን ሥልጣኔ ያዋለዱትን የፍልስፍና ስርዓቶች ፍሬ ሃሳቦቻቸው በግሩም ሁኔታ ከግሪክ ጀምሮ በእነ ፕሌቶ አልፎ እስከ ኒቼ በማብራራት፤ ፍልስፍናዊ ሃሳቦች እንዴት አድርገው ልዩ ልዩ የታሪክ ኩነቶችን ማለትም የትምህርት፣ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ እና የኪነጥበብ በአጠቃላይ የየዘመኑ ባህልን ቅርጽ እና አቅጣጫ መወሰን እንደቻሉ ያሰቃኘናል። ቀጥሎ ኢትዮጵያዊውን ሥልጣኔ (እሱ ያሬዳዊ ሥልጣኔ ብሎ የጠራውን) ያዋለደውን ድህረ

አክሱም ከያሬድ ጀምሮ ያለውን ፍልስፍናዊ ሥርዓት እንዴት የኢትዮጵያን የተጠቃሚነት ደረጃ የጎደለውን ባህል ሊቀርፅ እንደቻለ አሁንም በግሩም ሁኔታ ያብራራል። ከዚህ ሁሉ በሁዋላ ነው የበተዋህዶ ከበረ ሃሳብ የሚያመጣው።

እንግዲህ ፈላስፋው እጉዋለ የታሪክ ኩነቶች ፍሰትን በማጥናት ሳይሆን ታሪክ-ፍልስፍናን በማጥናት የታሪክ ሁኔታዎችን የምንረዳበት ድንቅ ዘዴን ነው ለኢትዮጵያውያን አስተዋውቆን ያለፈው የምለው በዚህ ምክንያት ነው። ምን ዋጋ አለው! ማንም ይህንን ዘዴ ያስተዋለ ያለ አይመስልም። በአሁኑ ሰዓት የመቀሌ ዩኒቨርሲቲው የፍልስፍና መምህር ብሩህ አለምነህ አልፎ አልፎ በሚጽፋቸው መጣጥፎች ይህን መንገድ ሲከተል አስተውላለሁ (የሔዋን አመጽ የሚል አዲስ አድማስ ላይ የወጣው ጽሑፉ ልብ ይለዋል)፤ ምንም እንኩዋ በሌሎች ጽሁፎቹ ላይ ከታሪክ-ፍልስፍና ይልቅ ወደ ታሪካዊ ኩነቶች ይበልጥ የሚያመዝን ቢሆንም።

2. የከፍተኛ ትምህርት ዘይቤ

ሁለተኛው የእጉዋለ የፍልስፍና መንገድ አበርክቶ ራሱ የመጽሐፉ አርዕስት ያደረገውን የትምህርት ዘይቤን ነው።

ትምህርት ማለት 1ኛ፣ 2ኛ፣ ... እያሉ 12ኛ ክፍልን ከጨረሱ በሁዋላ ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ ገብቶ ተመርቆ መውጣት አይደለም። ትምህርት ማለት የትምህርት ደረጃዎችን መቁጠር ሳይሆን፣ ሰው በሕይወት ሲኖር በዙሪያው ያሉትን ቁሳዊም ይሁን መንፈሳዊ ግብዓቶችን ወደ ራሱ ጥቅም ለማዋል የሚያስችለውን አቅም የሚገነባበት መሰላል ነው። ትምህርት ማለት ኮሌጅ በጥሻለሁ፣ ዶክትሬት ይገዬአለሁ፣ ለኑሮ የሚያስፈልጉኝን ዕውቀት እና ክህሎት ሰብስቤ ጨርሻለሁ ተብሎ የሆነ ጊዜ ላይ የምናቆመው ነገር አይደለም። እንደዚህ አይነት የትምህርት እሳቤ ለእንስሳት ብቻ ነው የሚሰራው።

"ወፎችን ተመልከቱ" የሚለው ብሂል፣ የትምህርት ዘይቤ ላልተረዱ ብቻ ነው የሚያገለግለው። አንዲት ወፍ ከዕንቁላል ከተፈለፈለች በሁዋላ ለጥቂት ሳምንታት ወይም ወራት በእናቷ እርዳታ ነው የምትኖረው። ከዚያ በሁዋላ እናትየዋ ልጇን ራስዋ የምትችልበትን መንገድ አብራ እየወደቀች እየተነሳች በመብረር ታስተምራታለች። ዋናውን በሕይወት ለመኖር የሚረዳትን ክንፍዋን እንዴት እንደምትጠቀምበት ካስተማረቻት በሁዋላ ከጠላት ደግሞ ራሷን እንዴት እንደምትጠብቅ ታስተምራታለች። በዋናነት የወፊቱ የትምህርት ሕይወት እዚህ ላይ ያበቃል። ትምህርት ጨረሰች፤ ከጥንት ከአያት ቅድመ አያቶችዋ ጀምሮ ሲጠቀሙበት የነበረውን ተመሳሳይ አይነት ዕውቀት አጠናቅቃለች። አዲስ አይነት ትምህርት ይሁን ዘዴ አያስፈልጋትም። ምክንያቱም ከስዋ በፊት ከነበሩ ወፎች የተለየ ሂዎት አትኖርም። አትዘራም፣ አታጭድም አትወቃም። የተዘራ፣ የታጨደ፣ የተወቃ፣ የት እንደሚገኝ ግን ታውቃለች። ወይም ለማግኘት እየበረረች ትፈልጋለች። ህይወት ይቀጥላል- የማያቁዋርጥ የድግግሞሽ ህይወት።

የሰው ሕይወት ግን ፍፁም የተለየ ነው፤ ወይም ደግሞ የተለየ መሆን ይችላል። ምክንያቱም ሕይወቱን ባሻው አቅጣጫ ሊመራት ነፃ ፈቃድ አለውና። የሰው ኑሮ እና የአካባቢ ሁኔታ ከትውልድ ወደ ትውልድ ብቻ ሳይሆን የሚለያየው፣ በአንድ ሰው የህይወት ዘመን እንኩዋ ዳይናሚክሱ እጅግ ውስብስብ ነው። ስለዚህ ለሰው እያደገ በሚሄድ የዕውቀት ወይም የትምህርት ጎዳና ላይ መጉዋዝ ቅንጦት ሳይሆን የህይወት ዘይቤው መሰረታዊ ፍላጎት ነው።

የወፎችን ሂዎት መምረጥ ግን ይቻላል። በዚህም ለ3ሺህ ዓመታት በሞፈር እና ቀንበር እያረሱ መኖር ይቻላል። በሳርቤት እና በህድሞ ውስጥ መተኛት ይቻላል። በኩራዝ ብርሃን መኖር ይቻላል። በጠፍር አልጋ መተኛት ይቻላል። በአህያ እና በፈረስ መጉዋዝ ይቻላል። 16 ጊዜ አርግዞ 3 ልጆችን ያለ እናት ማሳደግ ይቻላል። አንድ አይነት እስከስታ እየወረዱ መደሰት መጨፈር፤ አንድ አይነት ሙሾ እያወረዱ ማልቀስ ማዘን ይቻላል። ይሄ ሁሉ ግን የወፎች(የእንስሳት) የትምህርት ዘይቤ ውጤት እንጂ የሰው የትምህርት ዘይቤ ውጤት አይደለም። "ሰው የሚማረው" ይላል ፈላስፋው እጉዋለ "ከዝቅተኛው ከእንስሶች ጋር የጋራ ከሆነው ሥነፍጥረታዊ ሁኔታ ወጥቶ በሐሳቡ ምኞት ስዕል መሠረት ከከፍተኛነት ከሙሉ የሰውነት ደረጃ ለመድረስ ነው።"

እጉዋለ ለዘመናት "አንዲት መጽሐፍን በመተርጎም" ላይ የተንጠለጠለውን እና ከወፎች እንድንማር አበክሮ የሚሰብከውን ትውፊታዊውን(የቅኔ ትምህርትን አይጨምርም) የእንስሳት የትምህርት ዘይቤ በዘመናዊው ትምህርት ዘይቤ እንዳይደገም በመሲጋት ለሰውነት የሚመጥን የትምህርት ዘይቤ ላይ እንድንደርስ ትምህርት ሊመራበት የሚገባ ትክክለኛውን የትምህርት ፍልስፍና አበርክቶልናል። ምን ዋጋ አለው! አሁንም ማንም ያስተዋለው ሰው ያለ

አይመስልም። ከጀርመን፣ ከሩሲያ፣ ከእንግሊዝ፣ ከቻይና፣ የተቀያየጠ የሰርተፊኬት ክምር የሚያስታቅፍ የትምህርት ሥርዓት ከመንግሥት ስርዓቶቹ ጋር አብሮ ይቀያየራል።

መፍትሄው ወደ ጀርመን፣ ሩሲያ፣ እንግሊዝ፣ ጃፓን፣ ቻይና... ወዘተ ከማማተር ወደ ፍልስፍና ማማተር ነው። ይህ ነው የእጉዋለ መንገድ። “ስለ ትምህርት የሚናገር ሰው ሁሉ ሶስት ጥያቄዎችን ለመመለስ አስቀድሞ መዘጋጀት አለበት።” ያለበለዚያ ይለናል እጉዋለ፣ “ነገሩ ፍሬቢስ እንደሚሆንበት ያስፈራዋል። እነዚህ ሶስት መሰረታዊያን ጥያቄዎች የሚቀጥሉት ናቸው። ምን፤ለምን፤እንዴት፤ የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ በመካከላቸው ግኑኝነት ያላቸው ናቸው። ትምህርት ሲባል ምንድር ነው፤ ለምን ወይስ ምነ ዓላማ ማገልገል ይገባዋል። እሊህ ሁለት ጥያቄዎች ሰው ምን መሆን እንደሚገባው እንመራመር ዘንድ በቀጥታ ወደ ስነ-ምግባር ፍልስፍና ሰፈር ይመሩናል። ስለዚህ የትምህርትን ባህርይና ዓላማ በትክክል አይቶ ለመወሰን በፍልስፍና ሲስተሞች ውስጥ ገብቶ ማሰብ ግድ ያስፈልጋል። ይህ ካልሆነ ነገሩን እንደምንበድለው አያጠራጥርም።”

የትምህርት ዘይቤ በዚህ መንገድ መመራት ሲኖርበት፤ “ትምህርት ምንድን ነው?” ብሎ ጠይቆ “የጀርመን እና የእንግሊዝ ተሞክሮ እንደሚያሳየን” ወደሚል መዝለል ምን አይነት ወራዳነት ነው?

እኔ ግን እላለሁ ዎፎችን አትመልከቱ! ፍልስፍናን ተመልከቱ! ወደ ምእራብ ተመልከቱ!

ተፈፀመ።

ሰላም

P.S. የከፍተኛ ትምህርት ዘይቤ መፅሃፍ ቅድመ-ክርስትና አከሱምን እና ምእራባዊውን ስልጣኔ ለማዋሃድ አልሞ ቢነሳ ኖሮ ምነ አይነት ቅርፅ እና ይዘት ይኖረው ነበር የሚለውን በሌላ ጊዜ በሌላ ርእስ ለመዳሰስ ፈልጌአለሁ።

CC: ብሩህ ዓለምነህ Eyasu Berento Mebrud Tsige